ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ Eth. $24.800 እርዳታ ፡ አግኝተናል ። እንዲ
ሁም ፡ ከግብጽ ፡ ናሽናል ፡ ካውንስል ፡ Eth. $12.500 ደርሶናል ። ስለዚ
ህም ፡ የማኅበሩ ፡ ወንድሞች ፡ የሆኑ ፡ ድርጅቶች ፡ ላደረጉት ፡ እርዳታ ፡
ከግርማዊነትዎ ፡ ፊት ፡ ምስጋና ፡ ሳላደርግ ፡ አላልፍም ።
ከዚህ ፡ በተረፈው ፡ Eth. $128.538 Eth. $19.700 ብቻ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ፊ
ት ፡ የምንሰበስበው ፡ ሰዳ ፡ ሲኖርብን ፡ Eth. $108.838 የማኅበሩን ፡ ጠቃ
ሚነት ፡ ከሚያምኑ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከሚገኙ ፡ ከተማ ፡ ነዋሪ ፡ ሕዝቦች ፡
የተሰበሰበ ፡ ነው ። ይህም ፡ የገንዘብ ፡ ሰብሰባ ፡ ክንውን ፡ ሥራውን ፡ ከጀመ
ርን ፡ ጀምሮ ፡ ማኅበሩ ፡ ባሳየው ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ የተገኘ ፡ ውጤት ፡ ነው ፡
ለማለት ፡ ይቻላል ።

የአዲስ ፡ አበባ ፡ ሕዝብ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ የሐሳብ ፡ ደጋፊነት ፡ ይህን፡
ለትውልድ ፡ የሚያልፍ ፡ የጋራ ፡ ቤት ፡ ተባብሮ ፡ በመሥራቱ ፡ ሲደሰትብ
ትና ፡ ሲኰራበት ፡ ይኖራል ። እንዲሁም ፡ በዚህ ፡ ማኅበር ፡ መሪነት ፡ የአ
ንድ ፡ ከተማ ፡ ሕዝብ ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ያለበትን ፡ ኀላፊነት ፡ በመገ
ንዘብ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ የጋራ ፡ ጥቅም ፡ በኅብረት ፡ ለመሥራት ፡ እንደሚ
ችል ፡ የጋለ ፡ ተስፋ ፡ አለን ። ከዚህ ፡ ማኅበር ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ተስፋ ፡
ወጣቶች ፡ ክፉንና ፡ በጎን ፡ በማወቅ ፤ በብርሃን ፡ ፋና ፡ እየተመሩ ፡ ለሀገራ
ቸው ፡ ታማኝና ፡ ዐዋቂ ፡ የትውልድ ፡ ራስ ፡ ለመሆን ፡ ለተቀደሰ ፡ ተግባር ፡
የሚዘጋጁበት ፡ እንዲሆን ፡ ነው ። ስለማኅበሩ ፡ አቋቋምና ፡ መሠረታዊ ፡
አሳብ ፡ ባጭሩ ፡ እናገራለሁ ። ይህ ፡ ማኅበር ፡ ዋና ፡ ፍላጎቱ ፡ የዓለምን ፡
ሕዝቦች ፡ ወገንና ፡ ባዕድ ፡ ሃይማኖትና ፡ ቀለም ፡ ሳይለይ ፡ ሁሉንም ፡ በአ
ንድ ፡ ላይ ፡ አስተባብሮ ፡ በማቀራረብ ፡ በመካከላቸው ፡ የወንድማማችነት፡
መንፈስ ፡ በመፍጠር ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የግል ፡ ጉዳዩንና ፡ ጥቅሙን ፡ ብቻ ፡
ሳይመለከት ፤ ለመላው ፡ ዓለም ፡ ሰላም ፡ የሚመች ፡ ሥራ ፡ የመሥራት ፡
መንፈስ ፡ እንዲያድርበትና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ በምድር ፡
ላይ ፡ ለማሳወቅ ፡ ነው ። ሰዎች ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ ተሰብስበው ፡ በፍቅር ፡
በመተሳሰር ፡ በመካከላቸው ፡ በጎ ፡ ምግባርን ፡ በመሥራት ፡ ሌሎች ፡ ወገ
ኖቻቸውንም ፡ ወደ ፡ በጎ ፡ ምግባር ፡ ለመምራት ፡ የሚያስቡትን ፡ መን
ፈስ ፡ በአእምሮዋቸው ፡ መቅረጽና ፡ ወጣቶች ፡ በእድገታቸው ፡ ሙሉ ፡
የማስተዋልን ፡ ችሎታና ፡ በዕውቀት ፡ የመስፋፋትን ፡ ዕድል ፡ እንዲያ
ገኙ ፡ መርዳት ፡ በማኅበራዊም ፡ ኑሮ ፡ ያለባቸውን ፡ ኀላፊነት ፡ ማሳወቅ ፡



የወጣት ፡ ወንዶች ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ማኅበር ፡ ዓይነተኛ ፡ ተግባሩ ፡ ነው ።
ይህ ፡ ማኅበር ፡ አገልግሎቱን ፡ በሚፈጽምባቸው ፡ በ፸፰ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ፡
አንድ ፡ ዐይነት ፡ ዓላማ ፡ አለው ። ይኸውም ፡ ወጣቶችን ፡ በአእምሮ ፡
ብሩህ ፡ በመንፈስ ፡ ጽኑ ፡ በአካላዊ ፡ ጥንካሬ ፡ ሙሉ ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡
ድርጁ ፡ አድርጎ ፡ በቀና ፡ መንገድ ፡ በመምራት ፡ ለአገራቸው ፡ ታማኝና ፡
መልካም ፡ ሕዝቦች ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

የወጣት ፡ ወንዶች ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ማኅበር ፡ ምንም ፡ በዓላማዊና ፡
በሥራው ፡ አመራር ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ ቢሆንም ፡ ሥራው ፡ የሚካሄደ
ውና ፡ የሚጠበቀው ፡ በዚያው ፡ ባለበት ፡ አገር ፡ በሚገኙ ፡ ሕዝቦች ፡ ነው።
ፕሮግራሙንም ፡ የሚያካሂደው ፡ ለሀገሩ ፡ በሚስማማ ፡ ዓይነት ፡ የሀገሩ ፡
ልማድና ፡ ባህል ፡ ሳይደመሰስ ፡ እንደ ፡ ሕዝቡ ፡ ሁናቴ ፡ እያየ ፡ ነው ።
ሥራው ፡ የሚካሄደው ፡ በዚያው ፡ ባለበት ፡ አገር ፡ እንደመሆኑም ፡
መጠን ፡ ለሥራው ፡ ማስኬጃ ፡ የሚሆነው ፡ ገንዘብ ፡ የሚገኘውና ፡ የሚ
ደግፈው ፡ ከዚያው ፡ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙ ፡ ሕዝቦች ፡ ነው ። ይህም ፡
በማኅበርተኝነት ፡ ከሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ በቀር ፤ ወጣቶች ፡ በዕውቀት ፡
የጐለመሱ ፡ መልካምና ፡ ታማኝ ፡ ሕዝቦች ፡ እንዲሆኑ ፡ ለመርዳት ፡ ቅን ፡
መንፈስና ፡ ፍላጎት ፡ ካላቸው ፡ አስተዋይ ፡ ሰዎች ፡ ከሚሰጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡
ችሮታ ፡ ነው ፤ ለምሳሌ ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ለሥራ ፡ ማስኬጃ ፡ ከወሰን
ነው ፡ ባጀት ፡ Eth. $35.843 ውስጥ ፡ ኒውዮርክ ፡ የሚገኘው ፡ የኢንቴርና
ሲዮናል ኮሚቴ ፡ Eth. $21.638 ርዳታ ፡ ሲሰጠን ፡ የቀረው ፡ Eth. $
14.205 ፡ የሞላው ፡ በሀገር ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙ ሕዝቦቹ ፡ በማኅበረተኛነ
ትና ፡ በስጦታ ፡ ካገኘነው ፡ ገንዘብ ፡ ነው ። ለአሁኑ ፡ ለያዝነው ፡ ዓመተ ፡ ዳ
ግም ፡ Eth. $48.495 ባጀት ፡ ተወስኗል ። ከዚህም ፡ ውስጥ ፡ የኢንቴርና
ሽናል ፡ ኮሚቴ ፡ Eth. $19.991 ፡ የሚረዳን ፡ መሆኑን ፡ አረጋግጠናል ።
ከዚህም ፡ የቀረውን ፡ Eth. $28.504 ግን ፡ ከሀገር ፡ ውስጥ ፡ ማግኘት ፡
ስላለብን ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ነዋሪ ፡ ሕዝቦች ፡ ባለፉት ፡ ዓመታት ፡ ላደረጉት
ችሮታ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋናችንን ፡ እያቀረብን ፤ እንደዚሁም ፡ በዚህ ፡ ዓ
መት ፡ ለዚህ ፡ ለማይቋረጥ ፡ አገልግሎታችን ፡ የተለመደ ፡ ልግስናቸውን ፡
እንዳይነሱን ፡ እንጠይቃለን ። በኒውዮርክ ፡ የሚገኘው ፡ የኢንተርናሲዮ
ናል ፡ ኮሚቴ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ እርዳታ ፡ በያመቱ ፡ ከማድረጉ ፡ በላይ ፡ የዚ

ህን ፡ ማኅበር ፡ ሥራና ፡ እንዲሁም ፡ ወጣቶቹን ፡ በእጅ ፡ ጥበብ ፡ ሥራ ፡ የማሠልጠን ፡ ልምድ ፡ ያላቸውን ሚስተር ፡ መርለን ፡ አ ፡ ቢሾፕ ፡ የተባሉ ፡ አሜሪካዊ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወጣት ፡ ወንዶች ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ እንዲያገለግሉ ፡ ሙሉ ፡ ደሞዛቸውን ፡ እየከፈለ ፡ የሚያሠራልን ፡ በመሆኑ ፡ ደግሜ ፡ አመሰግናለሁ ።

ሚስተር ፡ መርለን ፡ አ ፡ ቢሾፕ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከተላኩበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በዋናው ፡ ጸሐፊነት ፡ ሲያገለግሉ ፡ ለማኅበሩ ፡ ያስገኙት ፡ ሰፊ ፡ እርምጃና ፡ ቅን ፡ አገልግሎት ፤ ከፍ ፡ ያለ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ከሚያስመሰግናቸው ፡ ችሎታ ፡ ጋር ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ጠባይ ፡ የተመሉ ፤ እምነት ፡ ሊጣልባቸው ፡ የሚችሉ ፡ ሰው ፡ በመሆናቸው ፡ ስላደረጉት ፡ የሥራ ፡ አመራር ፡ በማኅበሩ ፡ ስም ፡ አመሰግናቸዋለሁ ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ዛሬ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ይህን ፡ አዲስ ፡ ሕንፃ ፡ ከፍ ፡ ላለ ፡ ሞያ ፡ እናውለው ፡ ዘንድ ፡ ለመልካም ፡ ሥራ ፡ ከፍቶ ፡ ሲመርቅልን ፤ በዚህ ፡ አዲስ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ከነበርንበት ፡ ሥፍራ ፡ የበለጠ ፡ አገልግሎት ፡ ለመስጠት ፡ የሚያስችለን ፡ መሆኑን ፤ በሚገባ ፡ እየተረዳን ፤ ከአሁን ፡ ቀደም ፡ እንሰጥ፡ ከነበረው ፡ ፕሮግራም ፡ በበለጠ ፡ ሁናቴ ፡ እያዘጋጀን ፡ ለወጣቶች ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ አገልግሎት ፡ እናካሂድበታለን ።

በዚህም ፡ አዲስ ፡ ሕንፃ ፡ ውስጥ ፡ እያንዳንዳችን ፡ በኀላፊነት ፡ ልንፈጽመው ፡ የሚገባን ፡ ተግባር ፡ ይኖርብናል ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ የመጀመሪያው፡ ዓመት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የሥራ ፡ ጊዜ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። ከግርማዊነትዎም፡ እርዳታ ፡ ጋር ፡ የሥራ ፡ ዕቅዳችን ፡ ሁሉ ፡ ከፍጻሜ ፡ እንደሚደርስልን ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ አለን ።

ይህን ፡ በአገራችን ፡ አዲስ ፡ የተቋቋመ ፡ ማኅበር ፡ ሥራውን ፡ በሚገባ ፡ በማካሄድ ፡ ከዚህ ፡ ደረጃ ፡ ለማድረስ ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ የመሪነት ፡ ተግባራቸውን ፡ ለፈጸሙ ፡ የሥራ ፡ ጓደኞቼ ፤ ለዲሬክተሮቹ ፡ ጉባኤ ፡ አባሎች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋናዬን ፡ አቀርባለሁ ፤ የጀግኖች ፡ ማኅበር ፡ ቤቱን ፡ አውሶን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ስንገለገልበት ፡ እንድንቈይ ፡ ስላደረገልን ፡ በማኅበሩ ፡ ስም ፡ ምስጋናዬን ፡ አቀርባለሁ ። ይህን ፡ ቤት ፡ ለማሠሪያ ፡ የሚሆን፡



ገንዘብ ፡ ለመሰብሰብ ፡ ሲደከምበት ፡ ለነበረው ፡ ሥራ ፡ የቅርብ ፡ ረዳት ፡ ሆነው ፡ ደንበኛውን ፡ አገልግሎት ፡ ለፈጸሙልን ፡ ለክቡር ፡ አቶ ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማና ፡ ለክቡር ፡ አቶ ፡ ምናሴ ፡ ለማ ፡ እንዲሁም ፡ ለአቶ ፡ አብደላ ፡ ሳሊም ፡ በዓጊል ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ምስጋናዬን ፡ አቀርባለሁ ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፤
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፤
ዕድሜ ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፤
ኢትዮጵያ ፡ በነፃነት ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

* * *

ለ) የማኅበሩ ፡ ጸሓፊ ፡ የምስተር ፡ መርለን ፡ ቢሾፕ ፡ ንግግር ፤

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ይህ ፡ አዲስ ፡ የወ. ወ. ክ. ማ. ሕንፃ ፡ መከፈት ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምረን ፡ በናፍቆት ፡ እንጠብቀው ፡ የነበረ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ቤት ፡ ዛሬ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ሲመርቁልንና ፡ በሩን ፡ ከፍተው ፡ ሲሰጡን ፡ ክብር ፡ አስገኙትውልናል ። በዚህም ፡ ትልቅ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ የአመራርዎን ፡ ሥርዓት ፡ አድንቀናል ። ለዜጎችዎም ፡ መልካም ፡ መስፋፋት ፡ በአደረጉት ፡ ብዙ ፡ ጠቃሚ ፡ ነገር ፡ ተደስተናል ።

ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ አስፈላጊ ፡ ለሆኑት ፡ ለዕውቀትና ፡ ለሰብአዊ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ዝንባሌዎ ፡ የሚያመዝን ፡ በመሆን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አስተያየትዎን ፡ እጅግ ፡ አደንቄያለሁ ። በአስተዋይነትዎም ፡ ከሚያቅዱዋቸው ፡ ሥራዎች ፡ ይኸው ፡ ዛሬ ፡ ውጤቱን ፡ እናያለን ። ከጥቂት ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ወ ・ ወ ・ ክ ・ ማ ・ ለኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ ሥራውን ፡ እንዲያካሂድ፡ ጠየቁ ። እኔም ፡ ለወጣቶች ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ ፕሮግራም ፡ እያካሄድኩ፡ ግርማዊነትዎን ፡ እንዳገለግል ፡ በመመረጤ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ደስታ ፡ ተሰምቶኛል ።

ይህን ፡ ወ. ወ. ክ. ማ. በአበባ ፡ ለማስጌጥ ፡ አስቀድሞ ፡ ማረስና ፡ መትከል ፡ ያሻል ። በጥበባዊ ፡ አስተያየትዎ ፡ ሥራው ፡ እንዲጀመር ፡ በመጠበቅ ፡ ዘሩን ፡ ተክለዋል ። በምርቃትዎም ፡ ወጣቱን ፡ አትክልት ፡ ውሃ ፡ አጠጥተውታል ፡ ለማኅበሩ ፡ ቤት ፡ የሚሠራበት ፡ ቦታ ፡ ሰጡ ፡ የቤቱን ፡

መሠረት ፡ ማዕዘን ፡ ድንጋይ ፡ አስቀመጡ ። በገንዘቡም ፡ ስጦታ ፡ ያደረጉት ፡ ልግስና ፡ ሌሎች ፡ እንዲከተሉ ፡ መልካም ፡ ምሳሌነትን ፡ ፈጠረ ፤ ለማድረግ ፡ ለሞከርነው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ምርቃትዎን ፡ አበረከቱልን ። በዚህ ፡ አዲስ ፡ ሕንፃ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ድንጋዮች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በጥንቃቄ፡ የተገነቡ ፡ ናቸው ። ሺው ፡ ድንጋዮች ፡ ከአሁን ፡ ቀደም ፡ የመጡትንና ፡ ሌሎችንም ፡ ወደፊት ፡ የሚመጡ ፡ ሺህ ፡ ወጣቶች ፡ ያመለክታል ።

ወ. ወ. ክ. ማ. በዓለም ፡ ዙሪያ ፡ የታወቀና ፡ በ፸፰ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ በሚሊዮን ፡ ለሚቈጠሩ ፡ ወጣቶች ፡ አገልግሎቱን ፡ የሚሰጥ ፡ ቢሆንም ፡ ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ቆራጭ ፡ የሆነ ፡ የበላይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የለውም ። በያንዳንዱ ፡ አገር ፡ የሚጠበቀውና ፡ የሚካሄደው ፡ በሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ጉባኤ ፡ ሆኖ ፡ የሚደገፈውም ፡ ወጣቶች ፡ በተድላ ፡ እንዲያድጉና ፡ ለሀገራቸው ፡ ታማኝ ፡ ሕዝቦች ፡ እንዲሆኑ ፡ ዕድልን ፡ ለመስጠት ፡ ከሚሹ ፡ ሰዎች ፡ በሚገኝ ፡ ገንዘብ ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

የወጣት ፡ ወንዶች ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ጉባኤ ፡ አባሎች ፤ ስለማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ መልካም ፡ አካሄድ ፡ በታማኝነት ፡ ለአደረጉት ፡ ድገፉ ፡ በተለይ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነውን ፡ የደስታ ፡ ስሜቴን ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ፊት ፡ ስገልጽ ፡ ትክክለኛ ፡ መሆኔ ፡ ይሰማኛል ፤ በክቡር፡ ኰሎኔል ፡ ታምራት ፡ ይገዙ ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ መሪነት ፡ ወ. ወ. ክ. ማ. ወደፊት ፡ በሰፊው ፡ ተራምዷል ። ይህም ፡ ዛሬ ፡ የሚመርቁት ፡ ሕንፃ ፡ ለቤቱ ፡ ማሠሪያ ፡ ለሚሰበሰበው ፡ ገንዘብ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ሆነው ፡ ከልብ፡ የሆነ ፡ የሥራ ፡ አገልግሎታቸውን ፡ ከሰጡት ፡ ከክቡር ፡ ኰሎኔል ፡ ክፍሌ፡ ዕርገቱ ፡ የተገኘ ፡ የሥራ ፡ ውጤት ፡ ነው ። በሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ጉባኤ ፡ አባሎች ፡ ትጋትና ፡ አመራር ፡ በሺህ ፡ በሚቈጠሩ ፡ ወዳጆቻችን ፡ እርዳታ፡ በወጣቶቻችን ፡ መካከል ፡ መልካም ፡ ጠባይንና ፡ ታማኝ ፡ ሕዝብነትን ፡ ለመመሥረት ፡ የሚያስችለው ፡ ይህ ፡ መታሰቢያቸው ፡ የሚሆን ፡ ሕንፃ ፡ ለፍጻሜ ፡ በቃ ። ለምለም ፡ መሬት ፡ የመልካም ፡ መከር ፡ እርሻ ፡ ሊሆን ፡ እንደሚችል ፡ ያህል ፡ ጥሩ ፡ ቤት ፡ ጥሩ ፡ ወ. ወ. ክ. ማ. አያደርግም ፡ በወ. ወ. ክ. ማ. ማሳ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ዘሮች ፡ በክበባችን ፡ አባል ፡ የሆኑና ፡ በሰው



ነት ፡ ማጠንከሪያ ፡ ሥራችን ፤ በእጅ ፡ ጥበብ ፡ ሥራ ፡ ክፍላችን ፤ በቲያትርና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ፕሮግራማችን ፡ ተካፋይ ፡ ሆነው ፡ የሚገኙ ፡ በሺህ ፡ የሚቈጠሩት ፡ ወጣቶች ፡ ናቸው ። እንዳስተዋልኩትም ፡ በሌላም ፡ ዓለም ፡ ከሚገኙ ፡ ወጣቶች ፡ ጋር ፡ በችሎታ ፡ እኩልነት ፡ ያላቸውና ፡ ባለብሩህ ፡ አእምሮ ፡ ታማኝ ፡ ወጣቶች ፡ መሆናቸውን ፡ ተመልክቻለሁ ። በዚህም ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ አለኝ ። ክበቦቻችንንና ፡ የስፖርት ፡ ክፍላችንን ፡ እንዲሁም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ፕሮግራማችንን ፡ ለተማሩ ፡ ወጣቶቻችን ፡ ማስፋፋትና ፡ ማካሄድ ፡ ብቻ ፡ ትምህርትን ፡ ለማግኘት ፡ ዕድል ፡ ሳይኖራቸው ፡ የቀሩትን ፡ በሺህ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሰዎችን ፡ ፍላጎት ፡ ለመሙላት ፡ ያለብንን ፡ ኀላፊነት ፡ አይቀንስልንም ።

እነዚህን ፡ ሰዎች ፡ ለመርዳት ፡ ወ . ወ . ክ . ማ . የትምህርት ፡ ክፍልና፡ ንግግሮች ፤ እንዲሁም ፡ የመወያያ ፡ ጊዜ ፡ እያዘጋጀ ፡ የዕለት ፡ ኑሮን ፡ መሠረታዊ ፡ መክፈቻ ፡ ለመስጠት ፡ አማርኛ ፡ ጽሕፈትና ፡ ንባብ ፤ ጤና ፡ አጠባበቅንና ፡ አመጋገብን ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ሁሉ ፡ በማስተማር ፡ ለመርዳት ፡ ይሞክራል ። በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ያለብንን ፡ ኀላፊነት ፡ የተሟላ ፡ ለማድረግ ፡ የምንችለው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሙሉ ፡ የሆነውን ፡ የሕይወት ፡ መንገድ ፡ የሚገኝበትን ፡ እርዳታ ፡ ለመስጠት ፡ ራሳችንን ፡ አሳልፈን ፡ በመስጠት ፡ ነው ። ወጣቶቻችንን ፡ ልንረዳ ፡ የሚገባንን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አልፈጸምንም ። ይህ ፡ አዲስ ፡ ቤት ፡ በውነቱ ፡ ሊረዳን ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ የወደፊት ፡ የሥራ ፡ ዐቅዳችን ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ድርጅት ፡ ይጨምራል ።

በሀገር ፡ ውስጥ ፡ ነዋሪ ፡ ለሆኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ የተደላደለ ፡ ችሎታ ፡ ስናገኝ ፡ በሥራችን ፡ ተመክተን ፡ አንደሰትም ። በሚሰጠው ፡ ትምህርትና ፡ አመራር ፡ የሕይወት ፡ ኑሮዋቸው ፡ የተሟላ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ በቤታቸውም ፡ ተደሳች ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ይሆናሉ ። የአዲስ ፡ አበባ ፡ ወ. ወ. ክ. ማ. እርሻ ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ እንዲሰጥ ፡ የተፈለገ ፡ እንደሆነ ፡ ማጠጣትና ፡ ማዳበር ፡ ያሻዋል ። አትክልተኛ ፡ ለሆኑት ፡ አብረውኝ ፡ ለሚሠሩ ፡ ሠራተኞች ፡ ምስጋና ፡ ማቅረብ ፡ ይገባኛል ፡ በቅን ፡ አገልግሎታቸው ፡ ውሃ ፡ አጠጥተዋል ፡ አዳብረውማል ። ወጣቶቹ ፡ ተክሎች ፡ አምረዋል ። ለመልካም ፡ መከር ፡ የሚታደሉ ፡ መሆናቸውም ፡ የማይጠረጠር ፡ ነው ። የወ. ወ. ክ. ማ. እርሻ ፡ ብዙ ፡ ምርት ፡ እንዲኖረው ፡ ለማድረግ ፡ የሠሩ ፡ ብዙዎች ፡ አሉ ። እነዚህም ፡ የተባሉት ፡ ሰዎች ፡ ጊዜያቸውን ፡

ሰጥተው ፡ ባይረዱን ፡ ኖሮ ፤ ወጣቶቹን ፡ ተክሎች ፡ ለማሳደግ ፡ ባልቻልንም ፡ ነበር ። በዚህ ፡ አዲስ ፡ ቤታችን ፡ ተጨማሪ ፡ ብዙ ፡ ወጣቶች ፡ ለመርዳት ፡ እንችላለን ። ዓላማችን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ ዕውቀት ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ እንዲያድግ ፡ ለመርዳት ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ለማድረግ ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ በመንፈስ ፡ በአካላዊ ፡ ጥንካሬ ፡ በአእምሮ ፡ እንዲደረጅ ፡ መርዳት ፡ ያሻናል ። ዓላማችን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ፈጣሪውን ፡ መስሎ ፡ እንዲያድግ ፡ ነው ፤ ማለት ፡ በእውነት ፡ ጠንካራ ፡ በአካባቢው ፡ ከሚገኘው ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ እንዲወጣው ፡ ነው ። የዚህም ፡ የመጨረሻው ፡ ውጤት ፡ ግብረ ፡ ገብነት ፡ ያለው ፡ ጠባየ ፡ መልካምና ፡ ፈጣሪውን ፡ ወዳጅ ፡ ለሀገሩ ፡ ታማኝ ፡ ለሌሎች ፡ መልካም ፡ ለማድረግ ፡ አዘውትሮ ፡ የመውደድ ፡ ልምድ ፡ ያለው ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ ነው ።

የወ. ወ. ክ. ማ. ሥራ ፡ ክንውን ፡ የሚገመተው ፡ በየጊዜው ፡ በሚያስገኘው ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ ነው ። ግርማዊነትዎ ፡ ይህን ፡ የወጣት ፡ ወንዶች ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ማኅበር ፡ የዚህን ፡ ትልቅ ፡ አገር ፡ ሕዝቦች ፡ ለታማኝነትና፡ ለመልካም ፡ ፍሬ ፡ የሚያዘጋጅ ፡ ሆኖ ፡ እንዲያገኙት ፡ የዘወትር ፡ ጸሎታችን ፡ ነው ።

* * *

ሐ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

የወጣት ፡ ወንዶች ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ማኅበር ፡ ለዓለም ፡ ወጣቶች ፡ አእምሮአቸውን ፡ በማጐልመስ ፡ ባሕሪያቸውን ፡ በማረም ፡ መንፈሳቸውን ፡ በማነቃቃት ፡ ባገራችን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተቋቁሞ ፡ ለማየት ፡ የነበረን ፡ ምኞት ፡ ተፈጽሞ ፡ ሕዝባችን ፡ ይህንን ፡ ታላቅ ፡ በዓል ፡ በሚያከብርበት ፡ በዛሬው ፡ ቀን ፡ ይኸንን ፡ አዲስ ፡ ሕንፃ ፡ ስንከፍት ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ እያለን ፡ ነው ። ይኸም ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በመከፈቱ ፡ ትምህርት ፡ የአእምሮና ፡ የአካል ፡ እድገት ፡ የሚገኝባቸው ፡ ፕሮግራሞች ፡ በወጣት ፡ ወንዶች ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ማኅበር ፡ አማካይነት ፡ እርግጠኛና ፡ ቀዋሚ ፡ በሆኑ፡ መሠረቶች ፡ ላይ ፡ እንዲመሠረቱ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የተደረገው ፡ ድካምና ፡ መሥዋዕትነት ፡ መልካም ፡ ፍጻሜ ፡ እንዳገኘ ፡ ሊቈጠር ፡ ይቻላል ። ይህ ፡ ማኅበር ፡ ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ ባለማሰብ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በውጭ፡



አገር ፡ በሥራም ፡ ሆነ ፡ በገንዘብ ፡ ረገድ ፡ ከብዙዎቹ ፡ እርዳታን ፡ በማግኘት ፡ የተቋቋመ ፡ ስለሆነ ፡ ለሕዝባችንና ፡ ለሌሎች ፡ ክርስቲያናውያን ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ የመንፈስ ፡ መበረታቻ ፡ ሆኖ ፡ ማገልገል ፡ ዐይነተኛ ፡ ተግባሩ ፡ ነው ። ወጣቶቻችን ፡ ክርስቲያናዊ ፡ በሆነ ፡ አሳብና ፡ ኀይል ፡ እየተመሩ ፡ እንዲያድጉ ፡ ላለን ፡ እምነት ፡ እውነተኛ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ። ይህ፡ ሕንፃ ፡ በመንበረ ፡ ጸባዖት ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ በትምህርት ፡ ሚኒስቴራችንና ፤ በመንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ በመሆኑ ፡ የሚገባውን ፡ ሥፍራ ፡ ይዟል ። ስለዚህ ፡ የሚፈጽማቸው ፡ ተግባሮች ፡ ላካባቢዎቹ ፡ ቦታዎች ፡ ተገቢ ፡ ሆነው ፡ እንዲገኙ ፡ እንመኝለታለን ።

ይህ ፡ ማኅበር ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ በመሆን ፡ በክርስቶስ ፡ ወንድማማችነትን ፡ ላገኘበት ፡ ከፍተኛ ፡ ሐሳብ ፡ ነዋሪ ፡ ምስክር ፡ ነው ። እንደ ፡ አውሮፓውያን ፡ አቈጣጠር ፡ ፲፰፻፶፭ ፡ ዓ.ም. የኢንተርናሲዮናል ፡ ወጣት ፡ ወንዶች ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ማኅበር ፡ የመጀመሪያውን ፡ ስብሰባ ፡ ካደረገበት ፡ ጀምሮ ፡ ባለው ፡ በመቶ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ ታላቅ ፡ ድርጅት ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ወደ ፡ ሰማኒያ ፡ በሚጠጉ ፡ አገሮች ፡ ከፍ ፡ ያለ፡ አገልግሎት ፡ መፈጸሙን ፡ ማስታወስ ፡ የተገባ ፡ ነው ። የቦርዱ ፡ አባሎችና ፡ ሰክሬታሪው ፡ ሚስተር ፡ ቢሾፕ ፡ ሥራውን ፡ በመምራቱና ፡ ሕንፃውን ፡ በማሠራት ፡ ባደረጉት ፡ አገልግሎት ፡ ደስ ፡ እንዳለን ፡ እንገልጣለን ። እግዚአብሔር ፡ ማኅበሩን ፡ እንዲረዳውና ፡ ሠራተኞቹን ፡ እንዲያከናውን ፡ እንመኛለን ።

# 485

የኦስትሪያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር፡ ክቡር ፡ ኮንት ፡ አሊቪዩ ፡ ሬዚጊዩ ፡ ግንቦት ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. ከእኩለ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ሲያቀርቡ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቆመው ፡ የተናገሩትና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

የነምሳ ፡ ፌዴራል ፡ ሬፑብሊክ ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ እንድሆን ፡ ወደ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የተሾምኩበትን ፡

ድብዳቤ ፡ ለማቅረብ ፡ ሲፈቀድልኝ ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የነምሳን ፡ ሕዝብና ፡ የመንግሥቴንም ፡ ምኞት ፡ ለመግለጽ ፡ ምክንያት ፡ በማግኘቴ ፡ ለእኔ ፡ ክብሬ ፡ ነው ።

ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ትውልድ ፡ ጀምሮ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በነምሳ ፡ መካከል ፡ የተሳሰረ ፡ የቀድሞ ፡ ወዳጅነት ፡ አለ ። የዚህም ፡ የወዳጅነት ፡ ምልክት ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መልካም ፡ ፈቃድዎ ፡ ሆኖ ፡ ነምሳን ፡ በጐበኟት ፡ ጊዜ ፡ የተከናነበችው ፡ ክብር ፡ በአገሬ ፡ ተወላጆች ፡ ልብ ፡ የማይረሳ ፡ ሆኖ ፡ ይኖራል ። ግርማዊነትዎ ፡ ነምሳን ፡ ለመጐብኘት ፡ ምክንያት፡ ባገኙበት ፡ ጊዜ ፡ የነምሳ ፡ ሕዝብና ፡ መንግሥቴ ፡ በግርማዊነትዎና ፡ በሕዝብዎ ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ግምት ፡ እንደነበረው ፡ ለማየት ፡ በመቻልዎ ፡ የምመሰገንበት ፡ ነው ።

እንዲሁም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለሚኖሩትና ፡ ለሚሠሩት ፡ ለነምሳ ፡ ተወላጆች ፡ ሁሉ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ ለተደረገላቸው ፡ የመልካም ፡ አድራጎት ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ ለማመስገን ፡ ይፈቀድልኝ ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የልብ ፡ ታዛዥነትና ፡ የጥልቅ ፡ ወሮታ ፡ መላሽ ፡ መሆናቸውን ፡ ከእኔ ፡ ይልቅ ፡ በእነሱ ፡ ስም ፡ ለመግለጽ ፡ መርሳትን ፡ አልፈቅድም ።

ንግግሬንም ፡ በመፈጸም ፡ በነምሳ ፡ ሕዝብና ፡ በመንግሥቴ ፡ ስም ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ አኗኗር ፡ የማቀርበውን ፡ መልእክት ፡ መልካም፡ ፈቃድዎ ፡ ሆኖ ፡ እንዲቀበሉኝ ፡ ልመናዬን ፡ አቀርባለሁ ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ክቡር ፡ ሚኒስትር ።

በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ዘንድ ፡ የኦስትሪያ ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ሆነው ፡ በመሾምዎ ፡ ከክቡር ፡ የኦስትሪያ ፡ ፌዴራል ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዴንት ፡ የተሰጠውን፡ የሹመት ፡ ድብዳቤ ፡ ከእጅዎ ፡ ስንቀበል ፡ በደስታ ፡ ነው ። በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የቈየውን ፡ ጽኑ ፡ የወዳጅነት ፡ መተሳሰሪያ ፡ ደስ ፡ በሚያሰኝ ፡ አኳኋን ፡ ገልጠውታል ። በተዋበች ፡ አገርዎ ፡ ያሳ



ለፍናቸው ፡ ቀኖች ፡ ምንም ፡ አጭር ፡ ቢሆኑ ፡ የኦስትሪያ ፡ ሕዝብ ፡ ለእኛና ፡ ለሕዝባችን ፡ ያለውን ፡ የወዳጅነት ፡ መልካም ፡ ስሜት ፡ ራሳችን ፡ ልንገነዘብባቸው ፡ ችለናል ። ኦስትሪያ ፡ ነፃነቷን ፡ እንድታገኝ ፡ የተመኘነውና ፡ የገለጽነው ፡ ጥልቅ ፡ ምኞት ፡ ተፈጽሞ ፡ በመስማታችን ፡ የኦስትሪያ ፡ መንግሥትና ፡ ሕዝብ ፡ ደስታ ፡ ተካፋዮች ፡ መሆናችንን ፡ ለመንግትዎ ፡ ቢገልጹልን ፡ ደስ ፡ ይለናል ።

ክቡርነትዎን ፡ በቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ በደስታ ፡ ስንቀበልዎ ፡ በኦስትሪያና ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛታችን ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ እውነተኛ ፡ ወዳጅነት ፡ የበለጠ ፡ ለማስፋፋትና ፡ ለማደርጀት ፡ በሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ የኛ ፡ የዘወትር ፡ በጎ ፡ አስተያየት ፡ የሚኒስትሮቻችንና ፡ የሕዝባችን ፡ እርዳታ ፡ የማይጓደልብዎ ፡ መሆኑን ፡ ልናረጋግጥልዎ ፡ እንወዳለን ። በመንግሥትዎና ፡ በኦስትሪያ ፡ ሕዝብ ፡ ስም ፡ ስለገለጡልን ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ እያመሰገንን ፡ እኛም ፡ በበኩላችን ፡ ለክቡር ፡ ፕሬዚዳንቱና ፡ ለኦስትሪያ ፡ ሕዝብ ፡ ደኅንነት ፡ ያለንን ፡ መልካም ፡ ምኞት፡ ከሰላምታችን ፡ ጋር ፡ እንዲያቀርቡልን ፡ እንጠይቅዎታለን ።

---

# 486

የፈረንሣይ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ አምባሳደር ፡ ክቡር ፡ ሙሴ ፡ ጃክ ፡ ባያን ፡ ግንቦት ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፬ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሹመት ፡ ድብዳቤያቸውን ፡ ሲያቀርቡ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቆመው ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ አምባሳደሩ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በፈረንሣይ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትነትዎ ፡ ዘንድ ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ እንድሆን ፡ የተሾምኩበትንና ፡ እንዲሁም ፡ ከእኔ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ሙሴ ፡ ሔንሪ ፡ የተጠሩበትን ፡ ድብዳቤ ፡ ለግርማዊነ

ትዎ ፡ ሳቀርብ ፡ ክብር ፡ ይሰማኛል ።
የግርማዊነትዎ ፡ የ፷፫ኛው ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ በሚከበርበት ፡ ዓመት፡
ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትነትዎ ፡ ዘንድ ፡ እንዳከናውን ፡ የተሰጠኝ ፡ ሥራ፡
ለእኔ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ሕሊናዬን ፡ የሚቀሰቅሰው ፡
ይሆናል ።
ዘግርማዊነትዎ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ብርሃናዊ ፡ መሪነት ፡ በኢትዮጵያ ፡
ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛትዎ ፡ ውስጥ ፡ የተከናወኑትን ፡ ግሩም ፡ የሆኑ ፡ እርም
ጃዎች ፡ ለማየት ፡ መላው ፡ ፈረንሣይ ፡ ከዚህ ፡ በዓል ፡ ተካፋይ ፡ ሳይሆን ፡
አይቀርም ።
ከጥቂት ፡ ወራቶች ፡ በፊት ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በፓሪስ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ፡
በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ የፈረንሣይ ፡ ሕዝብ ፡ ያደረገልዎ ፡ አቀባበል ፡ በኢትዮ
ጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥትና ፡ በፈረንሣይ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መካከል፡
ያለውን ፡ የፍቅር ፡ ግንኙነት ፡ በበለጠ ፡ ሳያደረጀው ፡ አልቀረም ።
ካለፉት ፡ ብዙ ፡ ዓመታቶች ፡ ጀምሮ ፡ የተገለጸውን ፡ ወዳጅነትና ፡
እንዲሁም ፡ ኢትዮጵያና ፡ ፈረንሣይን ፡ በታሪክ ፡ ያስተሳሰራቸውን ፡ አንድ
ነት ፡ በበለጠ ፡ ለማስፋፋት ፡ በተቻለኝ ፡ ሁሉ ፡ የምደክም ፡ መሆኔን ፡
በበኩሌ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ላረጋግጥልዎ ፡ እወዳለሁ ።
የፈረንሣይ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ሙሴ ፡ ረኔ ፡ ኰቲ ፡ ግርማዊ
ነትዎን ፡ ፈረንሣይ ፡ አገር ፡ በተቀበሉት ፡ ጊዜ ፡ ተሰምቷቸው ፡ የነበረውን፡
ደስታ ፡ እንድገልጽልዎ ፡ ታዝዣለሁ ። ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ የፈረንሣይ ፡
ሬፑብሊክ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ ጸጋ ፡ ለኢትዮጵያና ፡ ለሕዝብዎ ፡
ልማት ፡ ያላቸውን ፡ ምኞት ፡ እንድገልጽ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ የታዘዝኩትን፡
መልእክት ፡ ሳቀርብ ፡ ደስ ፡ እያለኝ ፡ ነው ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

## ክቡር ፡ አምባሳደር ።

በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ዘንድ ፡ የፈረንሣዊ ፡ ልዩ፡
መልክተኛና ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ሆነው ፡ በመሾምዎ ፡



ከክቡር ፡ የፈረንሣዊ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የተሰጠዎትን ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤ ፡
ከእጅዎ ፡ ስንቀበል ፡ በደስታ ፡ ነው ።
ከርስዎ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ የተከበሩ ፡ አምባሳደር ፡ የተጠሩበትን ፡
ደብዳቤ ፡ በምንቀበልበት ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሙሴ ፡ ሔንሪ ፡ በፈረንሣዊና ፡
በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛታችን ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ መግባባ
ትና ፡ መተባበር ፡ በበለጠ ፡ ለማጽናትና ፡ ለማስፋፋት ፡ ያደረጉትን ፡ መል
ካም ፡ አገልግሎት ፡ ሳናስታውስ ፡ አናልፍም ።
የፈረንሣዊን ፡ መናገሻ ፡ ከተማ ፡ በጐበኘንበት ፡ ባለፈው ፡ ቅርብ ፡
ጊዜ ፡ የፈረንሣዊ ፡ ሕዝብ ፡ ለኛና ፡ ለሕዝባችን ፡ ያለውን ፡ ፍቅርና ፡ የወዳ
ጅነት ፡ ስሜት ፡ እኛው ፡ ራሳችን ፡ አይተን ፡ ለመረዳት ፡ ችለናል ። ይህ ፡
በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የወዳጅነትና ፡ የመግባባት ፡ መን
ፈስ ፡ ባለፈው ፡ ዘመን ፡ የነበረውን ፡ ግንኙነታቸውን ፡ እንዳጸናው ፡ ሁሉ ፡
በሚመጣውም ፡ ዘመን ፡ በመካከላቸው ፡ የሚኖረውን ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙ
ነት ፡ እያስፋፋና ፡ እያደረጀ ፡ እንደሚሄድ ፡ ያለንን ፡ ምኞት ፡ ስንገልጽ ፡
ደስ ፡ ይለናል ። ክቡርነትዎ ፡ በፈረንሣዊና ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግ
ሥት ፡ ግዛታችን ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ጥንታዊ ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡
ለማጠንከር ፡ በሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ የኛ ፡ የዘወትር ፡ በጎ ፡ አስተያየት፡
የመንግሥታችንና ፡ የሕዝባችን ፡ እርዳታ ፡ እንደማይጓደልብዎ ፡ እናረጋግ
ጥልዎታለን ።
ለክቡር ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ረኔ ፡ ኰቲ ፡ የወዳጅነት ፡ ሰላምታችንንና ፡
እንደዚሁም ፡ ለፈረንሣዊ ፡ ሕዝብ ፡ ደስታና ፡ ብልጽግና ፡ ያለንን ፡ መል
ካም ፡ ምኞት ፡ እንዲገልጹልን ፡ እንጠይቅዎታለን ።

---

# 487

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በአባ ፡ ዲና ፡ የፖሊስ ፡ ከፍተኛ፡
መኰንኖች ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በአራተኛው ፡ ኮርስ ፡ ለሠለጠኑት ፡ ፷፪ ፡ እጩ ፡
መኰንኖች ፡ ግንቦት ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም. ከእኩለ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ዲፕሎም ፡ ሲሰጡ ፡ የተ
ናገሩት ፡ መሪ ፡ ቃል ።

ከዚህ ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ትምህርታችሁ ፡ ተቃንቶላችሁ ፡ ስት
ወጡ ፡ ከናንተ ፡ በፊት ፡ ለወጡት ፡ እጩ ፡ መኰንኖች ፡ የምስክር ፡ ወረቀ

ታቸውን ፡ በእጃቸው ፡ እንደሰጠናቸው ፤ ለእናንተም ፡ ይህን ፡ ስናደርግላ ችሁ ፡ ደስታችን ፡ የተቀነሰ ፡ አይደለም ። ያሳያችሁት ፡ የትምህርት ፡ ውጤ ታችሁን ፡ ከማሳየቱ ፡ በላይ ፡ የትራፊክና ፡ ሌሎችም ፡ ድርጅት ፡ በሰው ፡ ሕይወት ፡ ላይ ፡ የሚደርሰውን ፡ አደጋ ፡ ለመከላከል ፡ ዘመናዊ ፡ ጥበብ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ መጠበብና ፡ መሥራት ፡ እንዳለበት ፡ የሚያስረዳ ፡ ነው ። ባሳያችሁት ፡ ሁሉ ፡ ከተማሪ ፡ አስተማሪ ፡ መቅደም ፡ አለበት ፤ ሕዝባችን፡ ወደ ፡ እድገት ፡ ሲሄድ ፡ አስተማሪም ፡ ተማሪም ፡ ሆናችሁ ፡ ለመርዳት ፡ ዝግጁ ፡ ለመሆን ፡ መቅደም ፡ አለባችሁ ። የከተማችን ፡ ስፋት ፡ እያደገ ፡ የሕዝቡ ፡ በፍጥነት ፡ ወደ ፡ እድገት ፡ መራመድ ፡ እየተስፋፋ ፡ በመሄዱ ፡ መጠን ፤ የትራፊክም ፡ ደንብና ፡ ሥርዓት ፡ እየተጠና ፡ እንዲሠራበት ፡ የሚያስፈልግ ፡ ነው ።

የተማራችሁትን ፡ እንዳልዘነጋችሁና ፡ ተግባራችሁን ፡ ለመፈጸም ፡ ታማኝነታችሁን ፡ ላለማጉደል ፡ ወላዋይ ፡ ያልሆነ ፡ ቈራጥ ፡ መሆን ፡ አለባችሁ ። እንደዚህ ፡ ሆናችሁ ፡ የማትገኙ ፡ ከሆነ ፡ በሚገባ ፡ መሥራትን፡ እናንተው ፡ ተቃዋሚ ፡ ሆናችሁ ፡ ትገኛላችሁ ። ስለዚህ ፡ ትምህርታችሁን፡ በሥራችሁ ፡ ግለጡ ።

የመገናኛ ፡ ሚኒስቴራችን ፡ የመናገሻ ፡ ከተማችን ፡ ከንቲባ ፡ የፖ ሊስ ፡ ሠራዊት ፡ አዛዥ ፡ ለሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ ለተማራችሁት ፡ በሚመ ቸው ፡ አኳኋን ፡ ሐሳብ ፡ ስታቀርቡ ፡ ሕጉንና ፡ ደንቡን ፡ በመተባበር ፡ ተስማምተው ፡ እንዲሻሻል ፡ ለማድረግ ፡ ትእዛዛችንን ፡ እንሰጣለን ።

አሁን ፡ እዚህ ፡ በምሳሌ ፡ የታዩትን ፡ ስሕተቶች ፡ እንዲቀሩ ፡ በከተ ማውና ፡ በገጠርም ፡ ያሉት ፡ አደጋዎች ፡ እንዲቀነሱ ፡ ታላቅ ፡ ተስፋ ፡ አለን ። ከትምህርት ፡ ቤቱ ፡ በቴዎሪና ፡ በልማድ ፡ ያገኛችሁትን ፡ ከፍ ተኛ ፡ ትምህርት ፡ ወደፊት ፡ የሕዝባችንን ፡ ሰላምና ፡ ጸጥታ ፡ ለማከናወን፡ በምትደቀኑበት ፡ ሰዓት ፡ አስቸጋሪ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ቢያጋጥሟችሁ ፤ በማሰብና ፡ በማውጣት ፡ በማውረድ ፡ ሳትቸገሩ ፡ ሳትሰለቹ ፡ በቀላሉ ፡ በዘዴ ፡ በጥበብ ፡ በመራመድ ፡ የሕዝቡን ፡ ፀጥታ ፡ ሕይወቱንና ፡ ንብረ ቱን ፡ በዘመናዊ ፡ ጥበብ ፡ ለመጠበቅ ፡ እንድትችሉ ፡ የሚጠቅም ፡ መሆኑ ፡ የታመነ ፡ ነው ። ተንኰለኞች ፡ እንዳይቀድሟችሁ ፡ በጥበብ ፡ የተማራች ሁትን ፡ ትምህርት ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ለትምህርትም ፡ በመሽቀዳ ደም ፡ ትምህርትም ፡ ተምረናል ፡ ብላችሁ ፡ ትምህርት ፡ በቃን ፡ ሳትሉ ፡



ትምህርት ፡ እስከ ፡ ሕይወት ፡ ድረስ ፡ ፍጻሜ ፡ የሌለው ፡ ነው ። ለማፍረስ፡ ቀላል ፡ ነውና ፡ ያልተማሩ ፡ ተንኰለኞች ፡ እንዳይቀድሟችሁ ።

ማፍረስ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ነው ፤ መሥራት ፡ ከባድ ፡ ነውና ፡ በዚህ ፡ ያለባችሁ ፡ ኀላፊነት ፡ ታላቅ ፡ መሆኑን ፡ አሁን ፡ ባሳያችሁት ፡ በቂ ፡ አይደ ለም ። በሥራችሁና ፡ ትምህርት ፡ አልበቃንም ፡ በማለት ፡ በመትጋታችሁ፡ ነው ። ለዚህም ፡ እምነታችንና ፡ ተስፋችን ፡ የበረታ ፡ ነው ።

ባለፉት ፡ ጊዜያት ፡ ለጓደኞቻችሁ ፡ እንደተናገርነው ፤ ዛሬም ፡ ደግ መን ፡ ለናንተ ፡ ልናሳስባችሁ ፡ የምንወደው ፤ የፖሊስ ፡ ዋና ፡ ተግባሩ ፡ ለሀገሩና ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ መታመን ፡ ለሕዝቡ ፡ መታዘ ዝና ፡ የአባትነት ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ለፖሊስ ፡ እውነተኛ ፡ እንደማይና ወጽ ፡ ምሽግ ፡ ጽኑ ፡ መሆን ፡ ቢያስፈልግም ፤ ሕይወቱን ፡ በሌላው ፡ ቤዛ ፡ መስጠት ፡ ድረስ ፡ አርቆ ፡ መሄድ ፡ እንዳለበት ፡ እንድታውቁት ፡ አደራ ፡ እንላችኋለን ።

የዘመናዊው ፡ ፖሊስ ፡ ሥራ ፡ ሲገመት ፡ ቀላል ፡ ሆኖ ፡ የሚታይ ፡ አይደለም ። ሕዝባችን ፡ በትምህርት ፡ እያደገ ፡ መሄዱ ፡ በናንተው ፡ ላይ ፡ ሊሠራ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ተረድታችሁታል ፤ የመላው ፡ ሕዝብ ፡ ዕውቀት ፡ ባደገ ፡ መጠን ፡ የወንጀልም ፡ ጥበብ ፡ ሲራቀቅ ፡ ያለትምህርት ፡ ነው ። ፖሊሶች ፡ ግን ፡ ያንን ፡ ለማሸነፍ ፡ በትምህርት ፡ እንድትደረጁ ፡ አድርገ ናል ። ወንጀለኛን ፡ መያዝ ፡ ብቻ ፡ የማይበቃ ፡ በመሆኑ ፤ ወንጀል ፡ እንዳ ይሠራ ፡ በመከላከል ፡ የፖሊስ ፡ ኀይል ፡ መደራጀት ፡ የወንጀልን ፡ ሥራ ፡ ለመቀነስ ፡ ጠቃሚነቱን ፡ በትምህርታችሁ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ዋና ፡ አርእስት ፡ ሳትማሩ ፡ እንዳልቀራችሁ ፡ እርግጥ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ወጥታችሁ ፡ ሥራችሁን ፡ በምትጀምሩበት ፡ ጊዜ ፡ አይታችሁት ፡ የማታ ውቁ ፡ ያላሰባችሁት ፡ ብዙ ፡ አደጋና ፡ አስቸጋሪ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ይገጥሟ ችኋል ። ይህንንም ፡ ለመግጠምና ፡ ለማሸነፍ ፡ ትምህርትን ፡ ደገፋ ፡ አድ ርጎ ፡ የራስን ፡ ጥቅምና ፡ ደስታን ፡ በመጥላት ፡ በምታደርጉት ፡ መሥዋዕ ትነታችሁ ፡ እንድትጥሩ ፡ አሁንም ፡ ደግመን ፡ አደራ ፡ እንላችኋለን ። ትምህርታችሁን ፡ ጨርሳችሁ ፡ የምስክር ፡ ወረቀታችሁን ፡ እንድታገኙ ፡ በማስተማር ፡ የረዱንን ፡ የስዊድን ፡ መኰንኖችን ፡ ከልብ ፡ እናመሰግና ቸዋለን ።

# 488

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ግንቦት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከእኩለ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ፪ኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ የሚገኘውን ፡ የደጃዝማች ፡ ወንዲራድን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሲጐበኙ ፡ የተነገሩ ፡ ቃሎች ፤

ሀ) የትምህርትና ፡ የሥነ ፡ ጥበብ ፡ ም/ሚኒስትር ፡ የክቡር ፡ አቶ ፡ አካለ ፡ ወርቅ ፡ ሀብተ ፡ ወልድ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ይህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የተመሠረተው ፡ በ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነው ። ሊቋቋም ፡ የቻለውም ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ፪ኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተማሪዎች ፡ በዚህ ፡ አካባቢ ፡ የሚገኙትን ፡ ወገኖቻቸውን ፡ በትርፍ ፡ ጊዜያቸው ፡ ለማስተማር ፡ ባደረጉዋቸው ፡ ቅን ፡ መንፈስና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ትጋት ፡ ነው ። በወጣቶችዎ ፡ በተማሪዎቹ ፡ ትጋት ፡ ግርማዊነትዎ ፡ አሁን ፡ ፎቶግራፉዋን ፡ ካያት ፡ እጅግ ፡ አነስተኛ ፡ ከሆነች ፡ ከአንድ ፡ ትንሽ ፡ ጐጆ ፡ ውስጥ ፡ ተጀመረ ። የተማሪዎቹ ፡ ብዛትና ፡ ትጋት ፡ በመታየቱ ፡ ምክንያት ፡ ወደዚህ ፡ ቤት ፡ እንዲዛወር ፡ ተደርጎ ፡ በየጊዜው ፡ በግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ ፈቃድና ፡ ችሮታ ፡ ይህ ፡ ታላቅ ፡ ቤት ፡ ተሠርቶ ፡ ተማሪዎቹ ፡ አሁን ፡ ፫ሺህ ፡ ሲሆኑ ፡ ከነሱ ፡ ፺ ፡ ሴቶች ፡ ይገኙበታል ።

እዚህ ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ የቻለበትን ፡ ምክንያት ፡ ለማመልከት ፡ የደፈርኩት ፡ በነዚህ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ባስተማራቸው ፡ ከዚያው ፡ ከተማሪ ፡ ቤት ፡ በወጡ ፡ ኢትዮጵያውያኖች ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ ነው ። ደግሞ ፡ ከማንኛውም ፡ ይህን ፡ ከመሳሰሉ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ እንደ ፡ አምኃ ፡ ደስታና ፡ እንደዚሁ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ የሚመሩ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ከሌሎች ፡ ይልቅ ፡ የበለጠ ፡ ፍሬ ፡ መስጠታቸውን ፡ የትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ባለሥልጣኖችና ፡ አማካሪዎች ፡ የመሰከሩት ፡ ነገር ፡ ነው ።

እነዚህ ፡ የደጃዝማች ፡ ወንድ ፡ ይራድ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መምህራኖች ፡ ብዙዎቹ ፡ ከዚያው ፡ ከቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ፪ኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የወጡ ፡ ናቸው ። ትምህርት ፡ ቤቱንም ፡ የሚመራው ፡ አቶ ፡ ማሞ ፡ ወልደ ፡ ሰንበት ፡ በጠላት ፡ ጊዜ ፡ ዘመዶቹን ፡ ፋሽስት ፡ ገድሎ



በት ፡ ካንድ ፡ የመንደር ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሲማር ፡ ቈይቶ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ሲመለሱ ፡ በ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ.ም. ትምህርት ፡ ጀምሮ ፡ አሁን ፡ አለበት ፡ ደረጃ ፡ የደረሰ ፡ ነው ።

ጅማ ፡ ከተማ ፡ በአስተማሪነት ፡ ከተቀጠረ ፡ በኋላ ፡ ፬ ፡ ዓመት ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ፪ኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እየተማረ ፡ በዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ያስተምር ፡ ነበር ። በጠቅላላው ፡ በዚሁ ፡ ክፍል ፡ አስተማሪ ፡ ሆነህ ፡ ልምምድ ፡ ብታደርግ ፡ ይሻላል ፡ በማለት ፡ የዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መሪ ፡ እንዲሆን ፡ ተደረገ ። ተማሪ ፡ ቤቱ ፡ ሲሠራ ፡ በጨረታ ፡ ወጥቶ ፡ ጨረታ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ በቀጥታ ፡ እሱ ፡ በቁጠባ ፡ መሐንዲሶች ፡ እየረዱት ፡ እንዲያሠራ ፡ ተደርጎ ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የሚያየው ፡ ቤት ፡ በጨረታ ፡ ከወጣው ፡ ከግማሽ ፡ ባነሰ ፡ ገንዘብ ፡ የተሠራ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ነው ።

ይህ ፡ ሜዳ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ አጥር ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ቤት ፡ የተሠራው ፡ የሚበልጠው ፡ በተማሪዎችና ፡ በነዚህ ፡ በመምህራኖች ፡ እርዳታ ፡ ስለሆነ ፤ በግርማዊነትዎ ፡ ፊት ፡ እንዳመሰግን ፡ እንዲፈቀድልኝ ፡ እለምናለሁ ።

አሁንም ፡ በመምህራኑና ፡ በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ መሪ ፡ ላይ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ አስተያየት ፡ አደራ ፡ የተጣለባቸው ፡ መሆኑን ፡ ዛሬም ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ፊት ፡ ባለፈውም ፡ ጊዜ ፡ ደጋግሜ ፡ ነግሬአቸዋለሁ ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መሪ ፡ ቃል ።

አሁን ፡ ይኸው ፡ አደራ ፡ ከሰጠነው ፡ የበላያችሁ ፡ የሰማነው ፡ ቃል ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘን ፡ ነው ። ከመጀመሪያ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ እስካለንበት ፡ ጊዜ ፡ ዋናው ፡ ዓላማችን ፡ ተማሪም ፡ አስተማሪም ፡ ከአገራችን ፡ እንዲወጣ ፡ ነው ። ይህ ፡ አሁን ፡ በኛ ፡ አገር ፡ ብርቅ ፡ ቢሆን ፡ በሌላው ፡ በቀደሙት ፡ አገሮች ፡ አስተማሪም ፡ ተማሪም ፡ ከነሱ ፡ ወጥቶ ፡ ከአገራቸው ፡ ተርፈው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ለማስተማር ፡ በቁ ።

ስለዚህ ፡ ዋና ፡ ተስፋ ፡ የምንጥልበት ፡ መማር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ማስተማርንም ፡ ነው ። ሰው ፡ ራሱ ፡ ብቻ ፡ ማግኘት ፡ ጥቅሙ ፡ አይደለም ።

ጥቅሙ ፡ እንደሱ ፡ ላለው ፡ ለወንድሙ ፡ ማካፈል ፡ ነው ። ይኸም ፡ የኛ ፡ ቃል ፡ አይደለም ፡ የፈጣሪያችን ፡ ቃል ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ አሁን ፡ እናንተ ፡ አስተማሪ ፡ ሆናችሁ ፡ ይህም ፡ እንደዚህ ፡ በትጋት ፡ ተሠርቶ ፡ ስናይ ፡ ተቀዳሚ ፡ በመሆናችሁ ፡ ደስ ፡ ይለናል ፡ እንጂ ፡ ተከታዩ ፡ በሙሉ ፡ ተማሪውም ፡ አስተማሪውም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ እንዲሆን ፡ የምንተማመንበት ፡ ነገር ፡ ነው ። ባደረጋችሁት ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ አሰኝታችሁናል ። ሥራችሁን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይባርክላችሁ ፤ በርቱ ፤ ሌሎችም ፡ ወንድሞቻችሁ ፡ በዚህ ፡ በናንተ ፡ እንዲቀኑ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

# 489

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ተመርጠው ፡ የመጡትና ፡ ለመርከብ ፡ ትምህርት ፡ የታጩት ፡ ወጣቶች ፡ በተሰበሰቡበት ፡ ላይ ፡ ግንቦት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተናገሩት ፡ መሪ ፡ ቃል ።

አሁን ፡ በዚህ ፡ የተሰበሰባችሁ ፡ ስለመርከብ ፡ ትምህርት ፡ ለመመረጥ ፡ መሆኑን ፡ አውቃችሁታል ። የመርከብ ፡ ትምህርት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የትምህርትና ፡ የመንፈስ ፡ ኀይል ፡ እንደሚጠይቅ ፡ ታውቁታላችሁ ። ይህንን ፡ ትምህርት ፡ ለመከታተል ፡ በፈቃዳችሁ ፡ የመረጣችሁና ፡ ለጊዜው ፡ ፈቃዳችሁን ፡ ያልገለጻችሁ ፡ ለምርጫው ፡ ቀርባችኋል ።

የመርከብ ፡ ትምህርት ፡ ጠንካራ ፡ መንፈስና ፡ ዕውቀት ፡ እንደሚጠይቅ ፡ ሁሉ ፡ ምርጫውም ፡ ፈቃደኞችን ፡ ብቻ ፡ ሳይከተል ፡ ብርታትና ፡ ንቃት ፡ የሚታይባችሁን ፡ መምረጥ ፡ ያስፈልጋል ። የትምህርቱን ፡ ጠቃሚነት ፡ ዛሬ ፡ እናንተ ፡ ለመመዘን ፡ ዐቅማችሁና ፡ አስተያየታችሁ ፡ ስለማይፈቅድ ፡ በሚፈጸምባችሁ ፡ ምርጫ ፡ ደስ ፡ አይላችሁም ፡ ይሆናል ። ትምህርቱን ፡ ስትጀምሩት ፡ ግን ፡ ያሁኑ ፡ የቅሬታ ፡ ስሜታችሁ ፡ በደስታ ፡ እንደሚለወጥ ፡ እናምናለን ።

ከሃያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ወጣቶች ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለማስገባት ፡ የነበረው ፡ ችግር ፡ አይረሳም ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ልጆችን ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለማስገባት ፡ ይቻል ፡ የነበረው ፤ በማባበልና ፡ ግዴታንም ፡ እስከ ፡ እስራት ፡ በመጨመር ፡ ነበር ። አሁን ፡



ግን ፡ የገንዘብ ፡ ችሎታችን ፡ ያሰብነውን ፡ ሁሉ ፡ ሊያስፈጽመን ፡ ባለመቻሉ ፡ ቅር ፡ ከሚለን ፡ በቀር ፡ ሕዝባችን ፡ የትምህርትን ፡ ጠቃሚነት ፡ ተከታትሎ ፡ ስለደረሰበት ፡ የተማሪ ፡ ችግር ፡ የለብንም ።

በሥልጣኔ ፡ ወደ ኋላ ፡ ቀሩ ፡ ከተባሉት ፡ አገሮች ፡ አንድዋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነች ፡ የተባለችው ፡ ጥንታዊ ፡ የባሕር ፡ በርዋን ፡ በማጣትዋ ፡ መገናኛዋ ፡ በብረት ፡ መጋረጃ ፡ ስለተጋረደባት ፡ ነበር ።

ብዙ ፡ ዓመታት ፡ ከተደከመበት ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃዱ ፡ ሆኖ ፡ ዛሬ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የባሕር ፡ በሮችዋን ፡ ስታገኝ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ሳይሆን ፡ በባሕር ፡ በሮችዋ ፡ መገናኛዋን ፡ እያሰፋች ፡ እርምጃዋን ፡ መቀጠል ፡ አለባት ።

የባሕር ፡ በርዋን ፡ ለማስፋፋትና ፡ እርምጃዋን ፡ ለመቀጠል ፡ የምትችለው ፡ አንደኛው ፡ መሣሪያ ፡ ከናንተ ፡ ውስጥ ፡ ቴክኒካዊ ፡ ትምህርት ፡ ስለሆነ ፤ ለዚህ ፡ ለታሰበው ፡ ከፍተኛ ፡ ሥራ ፡ የተገባችሁ ፡ ሆናችሁ ፡ መገኘት ፡ አለባችሁ ።

ለአገር ፡ የሚቈይ ፡ ነገር ፡ ለመሥራት ፡ የሚቻለው ፡ የራስን ፡ የሰለት ፡ ደስታን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ትቶ ፡ ነው ። እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የራሱን ፡ የኑሮ ፡ ምኞት ፡ ብቻ ፡ የተከተለ ፡ እንደሆነ ፡ ለትውልድ ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ ማቈየት ፡ አይቻልም ። ታሪክ ፡ ክፉውንና ፡ ደጉን ፡ የሚቀበል ፡ ነጭ ፡ ወረቀት ፡ ስለሆነ ፤ የዕለትን ፡ ደስታ ፡ ከሰውነት ፡ ባሕርይ ፡ አጥፍቶ ፡ ለትውልድ ፡ የሚተላለፍ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ መጣደፍ ፡ ታላቅ ፡ አአስተዋይነት ፡ ነው ።

የእኛም ፡ መሪነት ፡ የእናንተም ፡ ወጣትነት ፡ ያልፋል ፡ ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ የማታልፍ ፡ ስለሆነች ፤ ኢትዮጵያዊ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ በዘመኑ ፡ የማያልፍ ፡ ሥራ ፡ መሥራትና ፡ ለትውልድ ፡ ማቈየት ፡ አለበት ። ተከታዩ ፡ ትውልድ ፡ ሊሻሻልና ፡ ሊራመድ ፡ የሚችለው ፡ በምናቈየው ፡ መሰላል ፡ ነው ።

አሁን ፡ እያንዳንዳችሁ ፡ ብንጠይቃችሁ ፡ አገራችንንና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችንን ፡ ለማገልገል ፡ እንመኛለን ፡ እንደምትሉ ፡ እናምናለን ። አገርን ፡ ማገልገል ፡ ማለት ፡ ከዚሁ ፡ ጀምሮ ፡ ስለሆነ ፤ የተመረጣችሁበት ፡ ሥራ ፡ ከዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ ሥራዎች ፡ አንዱ ፡ በመሆኑ ፡ የሚጣልባችሁ ፡ አደራና ፡ ኀላፊነት ፡ ትልቅ ፡ መሆኑን ፡ አለመዘንጋት ፡ ነው ።

መታዘዝን ፡ የማያውቅ ፡ ማዘዝን ፡ አያውቅም ፡ እንደሚባለው ፡ በዕ

ውቀትና ፡ በዕድሜ ፡ ለሚበልጡዋችሁ ፡ መምህራን ፡ ታዛዥነትን ፡ ለመፈጸም ፡ የመጀመሪያ ፡ ሥራችሁ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ኢትዮጵያ ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ በቅንነትና ፡ በታዛዥነት ፡ የታወቀች ፡ አገር ፡ ስለሆነች ፤ እናንተም ፡ ይህን ፡ ከአባት ፡ መውረስ ፡ የሚገባችሁን ፡ ቅንነትና ፡ ታዛዥነት ፡ በሥራ፡ እንድትገልጡ ፡ አደራ ፡ እንላችኋለን ።

እናንተ ፡ ለሌላው ፡ ዛሬ ፡ ብትታዘዙና ፡ ሰውነታችሁን ፡ ብታዋርዱ ፡ እናንተም ፡ ነገ ፡ በምታዙበት ፡ጊዜ ፡ ዋጋችሁን ፡ ስለማታጡ ፡ ጠቅላላ ፡ አካሄዳችሁ ፡ ራሳችሁንና ፡ አገራችሁን ፡ የሚያስከብር ፡ ይሆናል ።

---

# 490

የኢራን ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ክቡር ፡ ሚስተር ፡ ሁሴን ፡ ዲባ ፡ ሰኔ ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፭ ፡ ሰዓት ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ሲያቀርቡ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቆመው ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ንግግር ።

ከእኔ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ሙሴ ፡ ሞዛፋር ፡ አላም ፡ የተጠሩበትንና ፡ እኔም ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትነትዎ ፡ ዘንድ ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ እንድሆን ፡ ከተወደዱ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቴ ፡ ከሼህ ፡ ኢንሻህ ፡ የተሾምኩበትን ፡ ደብዳቤ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ሳቀርብ ፡ ክብር ፡ እየተሰማኝ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ስቀበል ፡ ከደስታ ፡ ጋር ፡ ነው ።

ከግርማዊነትዎ ፡ ዙፋን ፡ ፊት ፡ እግሬን ፡ ለማግባት ፡ በማስቀድም በትም ፡ ጊዜ ፡ ላስታውሰው ፡ የሚገባኝ ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የኖረውን ፡ ዕድለኛውን ፡ የተሳሰረ ፡ ወዳጅነትና ፤ እንዲሁም ፡ በጋራ ፡ ታሪኮቻችን ፡ ገጽ ፡ ውስጥ ፡ የመግባባት ፡ አከባበርን ፡ ነው።

እንደመተሳሰባችን ፡ ፈቃድ ፡ መሠረት ፡ በፍጥነት ፡ ለመቀራረብ ፡ ያላስቻለን ፡ ምክንያት ፡ የጊዜዎቹ ፡ ሁኔታዎች ፡ ናቸው ። ይህንንም ፡ ግንኙነት ፡ በበለጠ ፡ ለማስተማር ፡ ግርማዊነትዎና ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቴ ፡ በዚህ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነው ፡ ሰዓት ፡ በቅርብ ፡ የመቀራረብ ፡ ፈቃድ፡ እንዳላቸው ፡ የልቤን ፡ ለመግለጽ ፡ ምክንያት ፡ አጋጥሞኛል ።



ሁለቱን ፡ አገሮቻችንን ፡ በወዳጅነት ፡ የሚያስተሳስሩትን ፡ ምስክሮች ፡ ለማስፋፋትና ፡ ለማጠንከር ፡ ለተላክሁበት ፡ ተግባር ፡ አፈጻጸም ፡ የግርማዊነትዎ ፡ እርዳታ ፡ እንዳይለየኝ ፡ እለምናለሁ ፡ ይህንንም ፡ ከፍተኛ ፡ ክብር ፡ ያለውን ፡ ሥራ ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ዘንድ ፡ እንዳከናውን ፡ በመመረጤ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ።

ለታላቋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ልማት ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ለግርማዊትና ፡እንዲሁም ፡ በሙሉ ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ጸጋና ፡ ጤና ፡ እንዲሁም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ከፍተኛነት ፡ ያላቸውን ፡ ምኞት ፡ እንድገልጽና ፡ የወንድማማችነት ፡ ሰላምታ ፡ እንዳቀርብ ፡ ከተወደዱ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ታዝዣለሁ ።

❊ ❊ ❊

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ዘንድ ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ሆነው ፡ ከግርማዊ ፡ የኢራን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተሾሙበትን ፡ ደብዳቤ ፡ ከእጅዎ ፡ ስንቀበል ፡ ደስ ፡ ይለናል ። እንደዚሁም ፡ ከእርስዎ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ የተከበሩ ፡ ሚኒስትር ፡ የተጠሩበትን ፡ ደብዳቤ ፡ ከእጅዎ ፡ ስንቀበል ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ እየተስፋፋ ፡ እንዲሄድ ፡ ያደረጉትን ፡ እውነተኛ ፡ አገልግሎት ፡ ሳናስታውሰው ፡ አናልፍም ።

ክቡርነትዎን ፡ በቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ በደስታ ፡ ስንቀበልዎ ፡ የተላኩበትን ፡ ከፍተኛ ፡ መልክት ፡ ለመፈጸም ፡ በሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ ሁሉ ፡ የኛ ፡ የዘወትር ፡ እርዳታና ፡ በጎ ፡ አስተያየት ፡ እንደማይጓደልብዎ ፡ እናረጋግጥልዎታለን ። እንደዚሁም ፡ ጥንታዊነታቸው ፡ በታወቀው ፡ በሁለቱ ፡ አገሮቻችን ፡ መካከል ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ጸንቶ ፡ የቈየውን ፡ ግንኙነት ፡ ሁል ፡ጊዜ ፡ በመልካም ፡ አኳኋን ፡ ሲመራ ፡ የቈየው ፡ መግባባትና ፡ እውነተኛ ፡ ስሜት ፡ እየቀጠለ ፡ እንዲሄድ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

ግርማዊ ፡ የኢራን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለእኛ ፡ ለራሳችን ፡ ለቤተ ፡ ሰባችንና ፡ ለሕዝባችን ፡ ስለ ፡ ላኩት ፡ የወንድማማችነት ፡ ሰላምታ ፡ ምስጋናችንን ፡ እንዲያቀርቡልንና ፡ እኛም ፡ በበኩላችን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡

ባላቸው ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ መሪነት ፡ ለሚተዳደረው ፡ ለታላቁ ፡ የኢራን ፡ ሕዝብ ፡ ብልጽግናና ፡ ደኅንነት ፡ ያለንን ፡ የልብ ፡ ምኞት ፡ ለገናናው ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥትዎ ፡ እንዲገልጹልን ፡ እንጠይቅዎታለን ።

---

# 491

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጅማን ፡ ለ፫ኛ ፡ ጊዜ ፡ ለመጐብኘት ፡ ሰኔ ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከጧቱ ፡ በ፫ ፡ ሰዓት ፡ ተሩብ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አየር ፡ መንገድ ፡ አውሮፕላን ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ተነሡ ፤ በ፬ ፡ ሰዓት ፡ ከ፳፭ ፡ ደቂቃ ፡ ጅማ ፡ ከተማ ፡ ደረሱ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ የክብር ፡ አቀባበል ፡ ተደረገላቸው ። በዚሁ ፡ ቀን ፡ በ፭ ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ እርሻ ፡ ኮሌጅ ፡ ሄደው ፡ ትምህርት ፡ ቤቱን ፡ ከጐበኙ ፡ በኋላ ፡ አዲስ ፡ የተሠራውን ፡ የኮሌጁን ፡ ሕንፃ ፡ መርቀው ፡ ሲከፍቱ ፡ የሚከተሉት ፡ ንግግሮች ፡ ተደረጉ ።

ሀ) የእርሻ ፡ ሚኒስትሩ ፡ የክቡር ፡ ባላምባራስ ፡ ማኅተመ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ መስቀል ፡ ንግግር ።

ይህን ፡ የርሻ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለመመረቅ ፡ ዛሬ ፡ የግርማዊነትዎ፡ እዚህ ፡ መገኘት ፡ ለበዓሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ውበትና ፡ ግርማ ፡ ከመስጠቱም ፡ በላይ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የግብርና ፡ ሥራ ፡ ለማስፋፋት ፡ ያለውን ፡ ሰፊ ፡ ሐሳብና ፡ ፕሮግራም ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ። ለኢትዮጵያ ፡ እድገትና ፡ ልማት ፡ ግርማዊነትዎ ፡ አስቦ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ከሚከታተላቸው ፡ በዘመነ ፡ መንግሥትዎ ፡ ከተፈጸሙትና ፡ ከሚከናወኑት ፡ አያሌ ፡ ከፍተኛ ፡ ሥራዎች ፡ ይህ ፡ አንደኛው ፡ ነው ።

ከዛሬ ፡ ፫፻ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ ፍራንሲዋ ፡ ባኰን ፡ የሚባል ፡ የእንግሊዝ ፡ ፈላስፋ ፡ ረጅም ፡ ሐተታ ፡ የሚያሻውን ፡ ቃል ፡ በማጠቃለል ፡ ማወቅ ፡ ኀይል ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ተናግሮአል ። ይህም ፡ ሊካድ ፡ የማይቻል ፡ እውነት ፡ ነው ። ግርማዊነትዎም ፡ እንደዚሁ ፡ ያለ ፡ ትምህርት ፡ ዕውቀት ፡ የማይገኝ ፡ መሆኑን ፡ ያውቅ ፡ ስለነበረ ፡ በቀደምትነት ፡ ከተፈጸሙት ፡ ሥራዎት ፡ ለሀገራችንም ፡ ሆነ ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ የሚተርፈውን ፡ የእርሻ ፡ ሲሳያችንን ፡ ለማስፋፋት ፡ የእርሻ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የመጀመርያውን ፡ ፕላን ፡ እንዲይዝ ፡ አደረገ ። ጠንካራ ፡ ሆኖ ፡ የተመሠረተውም ፡ ፕሮግራም ፡ እነሆ ፡ በየቀኑ ፡ እፍጻሜው ፡ እየደረሰ ፡ በፊታችን ፡ ይታያል ። ከፍ ፡ ያለ ፡ ዕውቀት ፡ እንዲያገኙ ፡ ተማሪዎችን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ በመላክ ፡ ብቻ ፡ ሳይወሰን ፡ በሀገራችን ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ትምህርት ፡



ቤቶች ፡ እንዲከፈቱ ፡ ተደርጓል ። ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ የመጀመሪያው ፡ የእርሻ ፡ ትምህርት ፡ መስጫ ፡ ያምቦ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የዛሬ ፡ ፳፬ ፡ ዓመት ፡ ተመሠረተ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ግዴታ ፡ ሆኖበት ፡ በጠላት ፡ ወረራ ምክንያት ፡ ፭ ፡ ዓመት ፡ ቢቋረጥ ፡ ይህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ባለፈውም ፡ ሆነ ፡ ለመጪውም ፡ ጠቃሚነቱን ፡ አረጋግጧል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ የግርማዊነትዎን ፡ ሰፊ ፡ ፕሮግራም ፡ ለማከናወንና ከቀን ፡ እቀን ፡ እያደገና ፡ እየጨመረ ፡ የሚሄደውን ፡ የሕዝቡን ፡ ፍላጎት ፡ ለማጥገብ ፡ ከፍተኛ ፡ ዕውቀት ፡ የሚሰጥበት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በፍጥነት ፡ እንዲቋቋሙ ፡ ማድረግ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሆነ ። ጃንሆይም ፡ ይህንኑ ፡ በመመልከት ፡ ከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዲቋቋም ፡ ፈቅደው ፡ ተስማሚውን ፡ ቦታ ፡ የሚመርጥ ፡ አንድ ፡ ሚሲዮን ፡ አዘዙ ። በጥናቱና ፡ በመሰናዶውም ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እንዳጋጣሚ ፡ ሁሉ ፡ ከፖይንት ፡ ፎር ፡ ጋር ፡ ንግግር ፡ ተጀመረ ። ፕሮዣችንም ፡ ከፍጻሜ ፡ ይደርስ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ የርሻ ፡ ኮሌጅና ፡ የርሻ ፡ ቴክኒክ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ የሚቋቋሙበት ፡ ውል ፡ ተፈረመ ። ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ በሐረር ፡ ላይ ፡ የኮሌጁ ፡ ሕንፃ ፡ በመሠራት ፡ ላይ ፡ ሲገኝ ፡ ከታቀዱት ፡ የርሻ ፡ ቴክኒክ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ደግሞ ፡ በፕሮግራሙ ፡ ቀደምትነት ፡ የያዘው ፡ አንዱ ፡ ከ፫ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ ሥራውን ፡ በማካሄድ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ።

ይኸውም ፡ ሞገስ ፡ አግኝቶ ፡ ዛሬ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ የሚመረቀው ፡ ነው ። ይህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በጃንሆይ ፡ ልግስና ፡ በፖይንት ፡ ፎር ፡ መዋጮ ፡ ገንዘብና ፡ ችሎታ ፡ ባላቸው ፡ መምህራን ፡ እርዳታ ፡ ተቋቁሞ ፡ የሚመራ ፡ ነው ። ተማሪ ፡ ቤቱ ፡ ጂማ ፡ ላይ ፡ እንዲሆን ፡ የተመረጠው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታና ፡ ምክንያት ፡ ነው ። ከሁሉ ፡ በፊት ፡ ይህ ፡ ታላቅ ፡ ፕሮግራም ፡ በቶሎ ፡ ፍጻሜ ፡ የሚያገኝበትን ፡ ቦታ ፡ ጠየቀ ። ጂማ ፡ ማደስና ፡ ማበጃጀት ፡ የሚያስፈልጋቸው ፡ ብዙ ፡ ቤቶች ፡ ያለው ፡ በመሆኑ ፡ ለዚህ ፡ ሥራ ፡ ተመረጡ ፡ ስለዚህም ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ሥራውን ፡ ለመጀመር ፡ ቻለ ። ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ በየጊዜው ፡ ብዙ ፡ መሻሻል ፡ ስለተደረገ ፡ አዳዲስ ፡ ቤቶች ፡ አጥሮች ፡ የውሃ ፡ ጉድጓዶችና ፡ ሌሎችም ፡ እንዲሁ ፡ ከመደርጀታቸው ፡ በላይ ፡ ይህ ፡ ዛሬ ፡ የሚመረቀው ፡ ለ፻፷ ፡ ተማሪዎች ፡ መኝታ ፡ የተዘጋጀው ፡ ሕንጻ ፡ ተሠራ ።

ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ ጂማ ፡ ዋና ፡ ኤክስፖርታችን ፡ የሆነው ፡ የቡና ፡ ሀገር ፡ ትውልዱ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ብቻ ፡ ጂማን ፡ ለዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መቋቋም ፡ የሚያስመርጠው ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ፡ ለዚሁም ፡ ማስረጃ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ለሀገራችን ፡ ኤኮኖሚ ፡ ከፍተኛውን ፡ ደረጃ ፡ ይዞ ፡ የሚገኘውን ፡ ቡናችንን ፡ ለማሻሻል ፡ የሚያጠናና ፡ የሚመራመር ፡ በተለይ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ከትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ይገኛል ። ይህ ፡ የማጥኛና ፡ የመመርመሪያ ፡ ክፍል ፡ እስታሲዮን ፡ ኤክስፔሪማንታል ፡ ስለ ፡ ቡና ፡ ልማት ፡ ከፖይንት ፡ ፎር ፡ ጋር ፡ ካለን ፡ ፕሮግራም ፡ የጠበቀ ፡ ግንኙነት ፡ አለው ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ባለፉት ፡ ዓመታት ፡ በዚህ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በመልካም ፡ መግባባት ፡ ስለ ፡ ተፈጸሙት ፡ አያሌ ፡ ሥራዎች ፡ ሙሉ ፡ እርዳታቸውን ፡ ላደረጉልን ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ መስፍን ፡ ስለሺ ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ፊት ፡ ምስጋና ፡ እንዳቀርብ ፡ ይፈቀድልኝ ፡ ዘንድ ፡ እለምናለሁ ። እንዲሁም ፡ የትምህርትና ፡ የሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ላደረገልን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እርዳታ ፡ ምስጋና ፡ ይገባዋል ።

አስተዋይ ፡ በሆኑ ፡ ዲሬክተራቸው ፡ እየተመሩ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነውን ፡ ተግባር ፡ በየቀኑ ፡ የሚፈጽሙትንም ፡ መምህራኖች ፡ አገልግሎት ፡ ሳላስታውስ ፡ አላልፍም ። በጠቅላላው ፡ ከመዋጮውም ፡ ገንዘብ ፡ በስተቀር ፡ ችሎታ ፡ ያላቸውን ፡ ባለ ፡ ሞያዎች ፡ በመስጠት ፡ ባደረጉልን ፡ እርዳታ ፡ ለፖይንት ፡ ፎር ፡ ሚስዮን ፡ ምስጋናዬን ፡ አቀርባለሁ ።

ግ ር ማ ዊ ፡ ሆ ይ ።

አሁን ፡ የትምህርት ፡ ቤቱን ፡ ጉዳይ ፡ እቀጥላለሁ ። ይህ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ በሚገባ ፡ ተደራጅቶና ፡ ተቋቁሞ ፡ አልቆ ፡ ስለሚገኝ ፡ ለወደፊቱ ፡ ከሚመጣው ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ በመዋጮው ፡ ገንዘብ ፡ መከሄዱ ፡ ቀርቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥትን ፡ ባጀት ፡ ብቻ ፡ የሚመለከት ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ፖይንት ፡ ፎር ፡ አስፈላጊዎቹን ፡ መምህራኖች ፡ በመስጠት ፡ ሊረዳን ፡ ተስማምቷል ። ይህም ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ወደፊት ፡ ለሚቋቋሙት ፡ ተማሪ ፡ ቤቶች ፡ የሥራ ፡ መምሪያ ፡ መዝገብ ፡ ሊሆነን ፡ የሚችል ፡ ነው ።



አጋጣሚ ፡ በመሆኑ ፡ እንድናገር ፡ ሲፈቀድልኝ ፡ በዚህ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ የኮሌጅ ፡ ትምህርት ፡ በሚሰጥበት ፡ ክፍል ፡ ያምቦን ፡ የርሻ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የጨረሱ ፡ ወጣቶች ፡ መኖራቸውን ፡ እጠቅሳለሁ ። እነዚህም ፡ ተማሪዎች ፡ ሌሎችም ፡ የኀንንላቸው ፡ ባለሞያዎች ፡ ሆነው ፡ በመገኘት ፡ የተጣለባቸውን ፡ ተስፋ ፡ የሚፈጽሙና ፡ የኢትዮጵያ ፡ የርሻ ፡ ልማት ፡ ሥራ ፡ በሚገባ ፡ የሚመሩ ፡ እንደሚሆኑ ፡ አምናለሁ ። በውጭ ፡ አገር ፡ ከተማሩት ፡ በስተቀር ፡ ካገራችን ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ የወጡ ፡ በግብርና፡ ሥራ ፡ ከፍተኛ ፡ ሞያ ፡ ያገኙ ፡ ወጣቶች ፡ ቴክኒስያኖች ፡ አሉን ። በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ትምህርታቸውን ፡ የሚጨርሱና ፡ ከትምህርት ፡ ቤቶቻችንም ፡ የሚወጡ ፡ ልጆች ፡ እናገኛለን ። በዚህ ፡ አካሄድ ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ ፕሮግራማችን ፡ እየተሟላ ፡ ይሄዳል ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጥበብ ፡ ያገኙት ፡ ወጣቶች ፡ ዕውቀታቸውን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የተለመውን ፡ ፈር ፡ ተከታትለው ፡ መሥራት ፡ ስላለባቸው ፡ የርሻ ፡ ሥራ ፡ መስፋፋት ፡ ደንበኛ ፡ የሆነ ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታውን ፡ ይይዛል ። ይህም ፡ የርሻ ፡ ፕሮግራም ፡ ሙሉ ፡ የመሬትን ፡ ልማት ፡ ለማከናወን ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ፕሮጌዎችና ፡ ቅርንጫፎች ፡ አጣምሮ ፡ የያዘ ፡ መሆኑን ፡ እናውቃለን ። ለምሳሌም ፡ ሕዝብን ፡ ከበዛበት ፡ ወደ ፡ አነሰበት ፡ አገር ፡ ማዛወር ፡ ወዲህም ፡ ሀብት ፡ የሚገኝበትን ፡ አገር ፡ ሕዝቡ ፡ እየሠራ ፡ እንዲጠቀምበት ፡ ማድረግ ፡ በመሆኑ ፤ ከተደቀኑበት ፡ ሥራዎች ፡ አንደኛው ፡ ዓቢይ ፡ ተግባር ፡ መሆኑ ፡ አይዘነጋም ። በዚህም ፡ ፕሮግራም ፡ ፖይንት ፡ ፎር ፡ በኀብረት ፡ ለመሥራት ፡ ያቀደ ፡ መሆኑን ፡ አስታውሳለሁ ።

ወጣቶችን ፡ እያደር ፡ የርሻ ፡ ጥበብ ፡ ባገኙና ፡ ይህንንም ፡ በሚገባ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ባዋሉት ፡ ቁጥር ፡ የግብርና ፡ ሥራችንና ፡ የከብት ፡ ርቢ ፡ ሞያችን ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ ይዞ ፡ በአፍሪካና ፡ በሌላም ፡ ዓለም ፡ ከሚገባን ፡ ደረጃ ፡ ያደርሰናል ።

የሰው ፡ ሕይወትና ፡ መልካም ፡ ኑሮ ፡ የርሻ ፡ ጥገኞች ፡ ናቸው ። ላለፈውም ፡ ላሁኑም ፡ ሆነ ፡ ለመጭው ፡ ትውልድ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ ግብርና ፡ ሥራ ፡ የተቀደሰ ፡ የለም ። የዚህንም ፡ ተግባር ፡ በመፈ

ጾም ፡ የሚገኘው ፡ ደስታ ፡ የርሻን ፡ ትምህርት ፡ ባለ ፡ ውለታ ፡ የሚያደር
ገው ፡ ነው ።

ግ ር ማ ዊ ፡ ሆ ይ ።

በጣም ፡ ተወዳጅ ፡ የሆነው ፡ የግርማዊነትዎ ፡ አስተዋይነት ፡ መሥ
ራችነትና ፡ ልግሥና ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ አይረሱም ። የዚህን ፡ በመልካም ፡
አስተያየት ፡ የተጀመረውን ፡ ከፍተኛ ፡ ተግባር ፡ ፍጻሜ ፡ ለማየት ፡ ከዚህ ፡
የተሰበሰቡት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ረጅም ፡ ዕድሜና ፡ መል
ካም ፡ ጤና ፡ ከኔው ፡ ጋር ፡ የሚመኙ ፡ መሆናቸውን ፡ አምናለሁ ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡
ዕድሜ ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡
ኢትዮጵያ ፡ በነፃነቷ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

* * *

ለ) የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ዲሬክተር ፡ የሚስተር ፡ ሐው ፡ ኤፍ ፡ ራውስ ፡ ንግግር ።

ግ ር ማ ዊ ፡ ሆይ ።

ግርማዊነትዎ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱን ፡ ለመመረቅ ፡ ፈቅዶ ፡ በዛሬ
ዩቱ ፡ ዕለት ፡ በመካከላችን ፡ በመገኘቱ ፡ የዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አስ
ተማሪዎችና ፡ ተማሪዎች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደስታ ፡ ይሰማናል ። ግርማዊነትዎ ፡
የርሻን ፡ ጥቅም ፡ አስፈላጊነት ፡ ዐውቆ ፡ የርሻ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡
በኢትዮጵያ ፡ እንዲስፋፋ ፡ በማድረጉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋና ፡ እናቀርባለን ።
ይህም ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ የዚሁ ፡ ሥራ ፡ ተካፋይ ፡ በመሆኑ ፡ ኩራት ፡ ይሰ
ማናል ። ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የሚያደርገው ፡ እርምጃ ፡ እንዲቃናለት ፡ በማ
ንኛውም ፡ ረገድ ፡ አስፈላጊውን ፡ እርዳታ ፡ ላደረጉለት ፡ ለክቡር ፡ የእ
ርሻ ፡ ሚኒስቴርና ፡ በፖይንት ፡ ፎር ፡ ውስጥ ፡ የሥራው ፡ መሪ ፡ ሆነው ፡
ለረዱት ፡ ምስጋናችንን ፡ እናበረክታለን ። እንደዚሁም ፡ እርዳታቸው ፡
እርምጃውን ፡ ላቃናው ፡ ለክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ መስፍን ፡ ስለሺ ፡ ምስ
ጋና ፡ እናቀርባለን ። የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የእርሻና ፡ የቴክኒክ ፡



ኮሌጅ ፡ ባልደረቦች ፡ በየጊዜው ፡ በሰጡን ፡ ምክርና ፡ እርዳታ ፡ ተጠቅመ
ንባቻዋል ።

ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ከዶክተር ፡ ሔንሪ ፡ ጂ ፡ ቤኔት ፡ ጋር ፡ አብ
ረው ፡ ይህን ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ የጂማ ፡ የእርሻ ፡ ቴክኒክ ፡ ትምህርት ፡
ቤት ፡ ቦታ ፡ የመረጡትን ፡ ሰዎች ፡ ስናስታውስ ፡ ደስታ ፡ ይሰማናል ።
ይህ ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛት ፡ የእርሻ ፡ አገር ፡ ለመሆኑ ፡
ጂማ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። በአየሩ ፡ ምቾት ፡ ቮልካኒስ ፡
በሆነው ፡ ለም ፡ አፈሩ ፡ ምክንያት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለእርሻ ፡ ልማት ፡ ከፍ ፡
ያለ ፡ ተስፋ ፡ የሚጣልባት ፡ አገር ፡ ናት ። ባለፉት ፡ ሦስት ፡ ዓመታት ፡
መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ሰማኒያ ፡ ተማሪዎችን ፡ ሲቀበል ፡
ለተማሪዎችና ፡ ለአስተማሪዎች ፡ መኖሪያ ፡ ለመማሪያ ፡ ክፍልና ፡ ለሳይ
ንስ ፡ ምርመራ ፡ የሚሆኑ ፡ በቂ ፡ ቤቶች ፡ አልነበሩም ። ግርማዊነትዎ ፡
እነሆ ፡ እንደሚመለከተው ፡ በዘመናዊ ፡ ዐቅድ ፡ የተሠራው ፡ የመኝታ ፡
ቤት ፡ እስከ ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ልጆች ፡ ለመያዝ ፡ ችሎአል ። ይህም ፡ የተ
ማሪ ፡ ቤቱን ፡ እድገት ፡ በቅርብ ፡ ከተከታተሉት ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ደስታች
ንን ፡ እንድንካፈል ፡ አድርሶናል ።

ይህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ በዘመናዊ ፡ ዐቅድ ፡ የተሠራው ፡
መኝታ ፡ ቤት ፡ በጠቅላላው ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሃምሳ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ወጥቶበ
ታል ። እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ ቊጥራቸው ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ተማሪዎችን ፡ ለመ
ቀበል ፡ ምቾት ፡ ይገኝ ፡ ዘንድ ፡ የመማሪያና ፡ የሳይንስ ፡ ምርመራ ፡ ክፍ
ሎች ፡ ተጨምረዋል ። የትምህርት ፡ ቤቱም ፡ ፕሮግራም ፡ በሰባት ፡ መምህ
ራን ፡ ይካሄድ ፡ የነበረው ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ የሁለት ፡ ዓመት ፡ የኮሌጅ ፡
ትምህርት ፡ በመቀጠሉ ፡ የመምህራኑ ፡ ቊጥር ፡ ከሰባት ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡
አራት ፡ ደርሶአል ። ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የእርሻ ፡ ጥናትና ፡ ምርመራ ፡ የሚያ
ደርግበት ፡ ሁለት ፡ ጋሻ ፡ የሚሆን ፡ መሬት ፡ አለው ። አስፈላጊ ፡ ድርጅቶ
ችም ፡ ስለተገኙ ፡ የከብትና ፡ የዶሮ ፡ ርቢ ፡ ተጨማሪ ፡ ሆነዋል ። የቡናና ፡
የሰብል ፡ ሙከራ ፡ በልዩ ፡ ዐይነት ፡ አያያዝ ፡ እንዴት ፡ እንደሚያድጉና ፡
እንደሚደረጁ ፡ የሚጠናበት ፡ ዘዴ ፡ ተዘጋጅቷል ።

ግ ር ማ ዊ ፡ ሆ ይ ።

እነሆ ፡ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ዋና ፡ ፍሬዎች ፡ እነዚህ ፡ ወጣቶች ፡

ናቸው ። ግርማዊነትዎ ፡ በጕብኝቱ ፡ ላይ ፡ እንደሚመለከተው ፡ የሚታየው ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ ሁሉ ፡ ሊከናወንና ፡ ውጤቱ ፡ ሊያምር ፡ የቻለው ፡ እነዚህ ፡ ወጣቶች ፡ በክፍል ፡ የተማሩትንና ፡ በሳይንስ ፡ ምርመራ ፡ የተረዱትን ፡ በቅልጥፍናና ፡ በትጋት ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ስለአዋሉት ፡ ነው ። ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ አሁን ፡ ከደረሰበት ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ሲመለከተው ፡ ደስ ፡ እንደሚያሰኝ ፡ ተስፋ ፡ ብናደርግም ፡ ቅሉ ፡ ለታቀደው ፡ ለወደፊት ፡ እርምጃው ፡ ይህ ፡ ገና ፡ የመጀመሪያው ፡ ውጥን ፡ መሆኑ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ጥረታችንም ፡ ይህንኑ ፡ ለማከናወን ፡ ከሆነ ፡ ለእርሻ ፡ መሣሪያ ፡ ለሰብልና ፡ ለእጅ ፡ ሥራ ፡ አገልግሎት ፡ የሚውሉ ፡ በቂ ፡ ቤቶች ፡ ያስፈልጋሉ ። ደግሞም ፡ ለእጅ ፡ ሥራና ፡ ለሳይንስ ፡ ምርመራ ፡ የብርሃን ፡ ኃይል ፡ የሚሰጥ ፡ የተለየ ፡ የኤሌክትሪክ ፡ ሞተር ፡ ያስፈልጋል ። በጥቂት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ የማጥኛና ፡ የመመርመሪያ ፡ ቦታ ፡ በመሆኑ ፡ ቡናን ፡ በሚያመርቱ ፡ በዓለም ፡ ክፍሎች ፡ ዘንድ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ በጣም ፡ የሚያኮራ ፡ ፕሮግራም ፡ እንዲዘጋጅ ፡ ምኞታችን ፡ ነው ። የግርማዊነትዎ ፡ ግዛት ፡ የሆነችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሌላው ፡ የዓለም ፡ ክፍል ፡ ሊገኝ ፡ የሚቻለውን ፡ ሀገረ ፡ ትውልዱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሆነውን ፡ የከፋን ፡ ቡና ፡ ለመመርመርና ፡ የተሻለ ፡ ዕውቀት ፡ ለመግለጽ ፡ አዲስ ፡ ምዕራፍ ፡ ታስገኛለች ። በኢትዮጵያ ፡ ጫካ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የቡና ፡ ዓይነቶች ፡ ከፍሬአቸውም ፡ ምርጥነት ፡ በላይ ፡ በሽታ ፡ የማይቃወማቸው ፡ ስለመሆኑ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የታወቁ ፡ ይሆናሉ ።

ለማንኛውም ፡ የትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ መሠረቱ ፡ መጻሕፍት ፡ በመሆኑ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ በመስፋፋት ፡ እንዲጠቅመን ፡ እንደሚያደርግልን ፡ እንመኛለን ። ከዚህ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ትምህርታቸውን ፡ በየችሎታቸው ፡ ከፍጻሜ ፡ አድርሰው ፡ የሚወጡ ፡ የእርሻን ፡ ጥበብ ፡ የተማሩ ፡ ወጣቶች ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ግዛት ፡ በሆነችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተወዳጅ ፡ የሆነ ፡ ሕዝብዎን ፡ በግብርና ፡ በኩል ፡ የሚያገኘውን ፡ ልማት ፡ እንደሚያስተምሩት ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

የጥረታችን ፡ ዓላማዎች ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈሩ ፤ ለግርማዊነትዎ ፡ ግዛት ፡ ታማኞች ፡ የሆኑና ፡ አገልግሎታቸውን ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ዘር ፡ ልማት ፡ የሚያውሉ ፡ እነዚህ ፡ ወጣቶች ፡ ናቸው ። ይህ ፡ የእርሻ ፡



ቴክኒክ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ዘንድ ፡ ሞገስ ፡ አግኝቶ ፡ ተመርቆ ፡ ለተወዳጅ ፡ ሕዝብዎ ፡ የተቀደሰ ፡ አገልጋይ ፡ እንደሚሆን ፡ እምነታችን ፡ ፍጹም ፡ ነው ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፤
ዕድሜ ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፤
ኢትዮጵያ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

❊ ❊ ❊

ሐ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ከዛሬ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የተመሠረተው ፡ ይህ ፡ አዲሱ ፡ የጂማ ፡ የቴክኒካልና ፡ የእርሻ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እውነተኛውን ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ።

ዛሬ ፡ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ሕንፃዎች ፡ ተዘጋጅተው ፤ አስተማሪዎቹና ፡ ተማሪዎቹ ፡ ተሟልተው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የእርሻ ፡ ሥራ ፡ እየተስፋፋ ፡ እንዲሄድ ፡ የሚያነቃቃ ፡ የትምህርት ፡ ገበያ ፡ ሆኖ ፡ እናየዋለን ። የትምህርት ፡ ቤቱን ፡ የሥራ ፡ እርምጃ ፡ በየጊዜው ፡ በቅርብ ፡ እንከታተል ፡ ስለነበረ ፤ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ በሚመረቅበት ፡ በዛሬው ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ መገኘታችን ፡ ያለንን ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ የሚገልጥ ፡ ምልክት ፡ ነው ። በዚህ ፡ የምናየው ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ የሚያበረታታና ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ለመምህራኑና ፡ ለተማሪዎቹ ፡ ልንገልጽላቸው ፡ እንወዳለን ። በዚህ ፡ ባጭሩ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የተፈጸመው ፡ የሥራ ፡ እርምጃ ፡ በእውነቱ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነው ። ይህ ፡ የተደረገው ፡ የሥራ ፡ እርምጃ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሁል ፡ ጊዜም ፡ የእርሻና ፡ የከብት ፡ አገር ፡ እንደመሆንዋ ፡ መጠን ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ ከመጣው ፡ ልማዳችን ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ነው ።

እግዚአብሔር ፡ መሰል ፡ የሌለውን ፡ ፍሬያማ ፡ መሬትና ፡ ዝናሙንም ፡ አብዝቶ ፡ አትርፎ ፡ ስለ ፡ ሰጠን ፤ ኢትዮጵያ ፡ ከሌሎቹ ፡ ከአፍሪቃና፡ ከመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ እንድትልቅ ፡ አድርጓታል ። ለዚህም ፡ ልዩ ፡ ስጦታውና ፡ በረከቱ ፡ ዘወትር ፡ ከልባችን ፡ ልናመሰግነው ፡ ይገባናል ።

የቀደሙት ፡ አባቶቻችን ፡ ከብዙ ፡ ክፍለ ፡ ዘመናት ፡ ጀምሮ ፡ በያመቱ ፡ መሬትን ፡ በማረስና ፡ አዝመራን ፡ በመሰብሰብ ፤ ከብትን ፡ በማርባትና ፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ እንደሚገኙት ፡ አንዳንዶቹ ፡ ዕድል ፡ የለሾች ፡ ሳይሆን ፡ ረኃብ ፡ አጥቅቶት ፡ ለማያውቀውና ፡ ቁጥሩ ፡ በየጊዜው ፡ እየበዛ ፡ ለሚሄደው ፡ ሕዝባችን ፡ ምግብ ፡ በማስገኘት ፡ መልካም ፡ ልማድን ፡ መሥርተዋል ። ስለዚህ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለደኅንነትዋና ፡ ለሥልጣኔ ፡ እርምጃዋ ፡ ከማናቸውም ፡ ሀብት ፡ ይልቅ ፡ ከእርሻ ፡ በሚገኙ ፡ ሀብቶች ፡ የምትመካ ፡ ናት ። ዛሬ ፡ ከመንግሥታችን ፡ ያመት ፡ ገቢ ፡ ከአራት ፡ እጅ ፡ ሦስቱ ፡ እጅ ፡ ያህል ፡ የሚሆነው ፡ ከእርሻ ፡ የሚገኝ ፡ ነው ። እንዱስትሪዎቻችንን ፡ ለማስፋፋት ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነው ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ለምናስመጣቸው፡ መኪናዎች ፡ የሚከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ የምናገኘው ፡ ከእርሻ ፡ በሚገኙት ፡ ሀብቶቻችን ፡ ነው ። ኢትዮጵያ ፡ የምታፈራቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሰብሎች ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ በጣም ፡ ርቀው ፡ ባሉት ፡ የዓለም ፡ ገበያዎች ፡ ይገኛሉ ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ ባለፉት ፡ ቅርብ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ታላቅ ፡ እርምጃ ፡ ተደርጓል ።

ኢትዮጵያ ፡ ከጦርነቱ ፡ወዲህ ፡ ከሐያ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ይገኝ ፡ ያልነበረ ፡ ብዙ ፡ የእርሻ ፡ ሀብት ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ገበያዎች ፡ ለመላክ ፡ ችላለች ። ነገር ፡ ግን ፡ በትልቅ ፡ ሥራ ፡ ማስፋፋት ፡ ገና ፡ ወደፊት ፡ የሚፈጸም ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ አለ ። ከዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በትምህርት ፡ የተገኘውን ፡ ዘመናዊውን ፡ የቴክኒክ ፡ ዕውቀት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በተሰጠን ፡ በጥንታዊ ፡ የአፈርና ፡ የዝናም ፡ ሀብታችን ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ አለባችሁ ። ቀድሞ ፡ ይበቅል ፡ የነበረውን ፡ የእርሻ ፡ ሰብል ፡ ማብዛትና ፡ ማሻሻል ፡ ዋና ፡ ተግባራችሁ ፡ ነው ። ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣውን ፡ አዝመራችንን ፡ በዓይነትም ፡ ሆነ ፡ በብዛት ፡ እየጨመረ ፡ እንዲሄድ ፡ ማድረግ ፡ አለባችሁ ። የከብት ፡ ርቢም ፡ ዕውቀት ፡ በጥብቅ ፡ በመከታተል ፡ የከብቶቻችንን ፡ ዐይነት ፡ ማሻሻል ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ተፈጽሞ ፡ ሲገኝ ፡ ሁሉም ፡ የተሻሻለ ፡ ኑሮን ፡ በማግኘቱ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ራሷን ፡ የቻለች ፡ አገር ፡ መሆንዋን ፡ ማረጋገጣችን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ ለጎረቤቶቻችንና ፡ ርቀውም ፡ ለሚገኙት ፡ አገሮች ፡ የሚቸግራቸውን ፡ በማቅረብ ፡ ረዳታቸው ፡ ልንሆን ፡ እንችላለን ። ስለዚህ ፡ ከዚህ ፡ የእርሻ ፡ ትምህርት ፡



ቤት ፡ ወደፊት ፡ ትምህርታችሁን ፡ ጨርሳችሁ ፡ የምትወጡ ፡ እናንት ፡ ወጣቶች ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ የጥንቱን ፡ መልካም ፡ ልማድ ፡ ወራሾችና ፡ የከፍተኛ ፡ አደራ ፡ ተቀባዮች ፡ ሆናችኋል ።

ይህንን ፡ ጥንታዊውንና ፡ ከፍተኛውን ፡ ሥራ ፡ በመምረጣችሁ ፡ ትመሰገናላችሁ ፤ ትጠቀማላችሁ ። በዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ የቴክኒክ ፡ ኅብረት ፡ አድሚኒስትሬሽን ፡ ረዳትነት ፡ መንግሥታችን ፡ በሰጣችሁ ፡ ትምህርትና ፡ የሳይንስ ፡ ዕውቀት ፡ ይህንን ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣውን ፡ ልማድ ፡ እንደምትጠብቁትና ፡ የተጣለባችሁን ፡ አደራ ፡ እንደምትፈጽሙ ፡ እንተማመንባችኋለን ። የመረጣችሁትን ፡ ሥራ ፡ አጠንክራችሁ ፡ ያዙ ። በእርሱም ፡ ተመኩበት ፡ እንጂ ፡ ውርደት ፡ አይሰማችሁ ። ለኢትዮጵያና ፡ ለሰው ፡ ዘር ፡ ለከፍተኛው ፡ ጥቅም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተሰጠንን ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ ለማጐልመስ ፡ የምትጥሩ ፡ ሁኑ ።

ይህን ፡ የእርሻ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እኛ ፡ በምንመኘው ፡ ዓይነት ፡ ለማቋቋም ፡ የደከሙትን ፡ የእርሻ ፡ ሚኒስትራችንንና ፤ ደጃዝማች ፡ መስፍን ፡ ስለሺን ፤ ዶክተር ፡ ሎተር ፡ ብራዎንንና ፤ የኮሌጁን ፡ ዲሬክተር ፡ ሚስተር ፡ ራውክን ፤ በሥራቸው ፡ ደስ ፡ እንዳለን ፡ ከምስጋና ፡ ጋር ፡ ልንገልጥላቸው ፡ እንወዳለን ።

እንደዚሁም ፡ ይህ ፡ የእርሻ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ጉዳይ ፡ እንደተወጠነ ፡ መልካም ፡ ምክር ፡ በመስጠትና ፡ ሥራውን ፡ በማበረታታት ፡ ሲደክሙ ፡ የነበሩትን ፡ ሟቹን ፡ ዶክተር ፡ ሔንሪ ፡ ጐርዶን ቤኔትን ፡ ልናመሰግናቸው ፡ እንወዳለን ። እንደዚሁም ፡ በኢትዮጵያ ፡ የዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ኦፍ ፡ አሜሪካ ፡ የተራድኦ ፡ ሥራ ፡ ዲሬክተር ፡ ሆነው ፡ በመተባበርና ፡ በስምምነት ፡ ሥራውን ፡ ሲያካሂዱ ፡ የነበሩትን ፡ ሚስተር ፡ ማርቆስ ፡ ጐርዶንን ፡ ልናስታውሳቸው ፡ ይገባናል ።

ስለ ፡ መምህራኑም ፡ የእነርሱ ፡ አገልግሎት ፡ ዛሬ ፡ በዚህ ፡ ተገኝተን ፡ በምንመርቀው ፡ የእርሻ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በበለጠ ፡ እምነት ፡ ተከናውኗል ፡ ለማለት ፡ እንችላለን ። እነዚህና ፡ ወደፊትም ፡ ከዚህ ፡ የእርሻ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ትምህርታቸውን ፡ ጨርሰው ፡ የሚወጡት ፡ ተማሪዎች ፡ መምህራኖቻቸው ፡ ስለ ፡ ሰጡዋቸው ፡ እውነተኛና ፡ የሚያነቃቃ ፡ ትምህርት፤ ውለታ ፡ መላሾች ፡ ሊሆኑ ፡ ይገባል ።

# 492

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሰኔ ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ . ም የጂማን ፡ የእርሻ ፡ ቴክኒክ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከመረቁ ፡ በኋላ ፡ የእርሻ ፡ ሥራዎች ፡ በተግባር ፡ ወደ ሚከናወኑበት ፡ ቦታ ፡ ሄደው ፡ ሲጐበኙ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ።

ሀ) ሽብሩ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ የተባለ ፡ ተማሪ ፡ በተማሪዎቹ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ የተናገ ረው፡ ቃል ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ግርማዊነትዎ ፡ በዛሬዪቱ ፡ ቀን ፡ በመካከላችን ፡ ስለተገኙልን ፡ እኛ ፡ የእርሻ፡ ቴክኒክ፡ትምህርት፡ ቤት ፡ ወጣቶች፡ (ተማሪዎች)ለደስታችን፡ ወሰን፡ የለውም። ግርማዊነትዎ፡ በየጊዜው፡ ለኢትዮጵያ፡ ልማትና፡ እድገት፡ ከሚጥ ረው ፡ ጥረት ፡ ሁሉ ፡ አንደኛው ፡ ክፍል ፡ የዘመናዊ ፡ የእርሻ ፡ ዕውቀት ፡ መስፋፋት ፡ ነው ። በግርማዊነትዎ ፡ አሳቢነት ፡ ይህ ፡ የእርሻ ፡ ቴክኒክ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተከፍቶልን ፡ እነሆ ፡ በእርሻ ፡ ትምህርት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ እንገኛለን ። ግርማዊነትዎ ፡ እኛ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ በዕውቀት ፡ እንድንጐለምስ ፡ በየጊዜው ፡ የሚያደርገው ፡ ድካም ፡ ወሰን ፡ የለውም ። የግርማዊነትዎ ፡ ለእኛ ፡ መድከም ፡ ከእኛ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ ለኢ ትዮጵያ ፡ ውለታን ፡ ፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ ከማንኛውም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የማይ ሰወር ፡ ነው ። ይህም ፡ ውለታ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በተፈጥሮዋ ፡ የተሰጣትን ፡ ሀብት ፡ እንድንሠራበትና ፡ ፩ኛ ፤ ለወገኖቻችን ፡ ጥቅም ፡ እንድናደርገው ፤ ፪ኛ፤ ለኢትዮጵያ ፡ እድገት ፡ እንድናውለው ፡ መሆኑ ፡ ለሁላችንም፡ ግልጽ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

እኛ ፡ የእርሻ ፡ ቴክኒክ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተማሪዎች ፡ ይህንን ፡ ውለታ ፡ በሥራ ፡ ፍሬ ፡ ለመመለስ ፡ በመዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ነን ። ይህንን ፡ ውለታ ፡ ለመመለስ ፡ ዕድለኞች ፡ እንድንሆን ፡ የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ እንዲሆን ፡ የሁላችን ፡ ጸሎት ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በእርሻ ፡ ቴክኒክ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ ይህችን ፡ ታናሽ ፡ በረከት ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ለማበርከት ፡ ሞገስ ፡ ስለአገኘሁ ፡ ለደስታዬ ፡



ወሰን ፡ የለውም ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊነትዎ ፤
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ፤
ዕድሜ ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብዎ ፤
ኢትዮጵያ ፡ በነፃነቷ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

❊ ❊ ❊

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ወደፊት ፡ ልትሠሩት ፡ የሚገባችሁንና ፡ ያለፈውንም ፡ ሥራችሁን ፡ ቅድም ፡ በተናገርነው ፡ ቃል ፡ ገልጠንላችኋል ። መምህሮቻችሁ ፡ ያስተ ማሩዋችሁንም ፡ ትምህርት ፡ ተከትላችሁ ፡ አገራችሁ ፡ የምትሠለጥንበ ትን ፤ ወገናችሁ ፡ የሚረዳበትን ፡ ጠቃሚ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ተጣጣሩ ።

ያገራችሁ ፡ ባለዕዳዎች ፡ ናችሁና ፡ ያለባችሁን ፡ ከባድ ፡ ኃላፊነት ፡ እያሰባችሁ ፡ ትጋትንና ፡ ቅንነትን ፡ በመያዝ ፡ ለመጭው ፡ ትውልድ ፡ የሚሆን ፡ የሥልጣኔ ፡ ቅርስ ፡ ለማትረፍ ፡ ተሽቀዳደሙ ። የራስን ፡ ዕለ ታዊ ፡ ደስታ ፡ ትቶ ፡ ያገርን ፡ አገልግሎት ፡ ካልተመለከቱ ፡ በብዙ ፡ በኩል ፡ ባለዕዳ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

ይህን ፡ አውቃችሁ ፡ አገራችሁ ፡ ለምትጠቀምበት ፡ ተግባር ፡ ሁሉ ፡ ረዳቶች ፡ ሆናችሁ ፡ የተገኛችሁ ፡ እንደሆነ ፤ ለእኛም ፡ ውለታ ፡ መላሾች ፤ ላገራችሁም ፡ አገልጋዮች ፡ መሆናችሁ ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ።

ውለታ ፡ መመለስ ፤ አገርን ፡ በቅን ፡ ሕሊና ፡ ማገልገልና ፡ ወገንን ፡ ከልብ ፡ መርዳት ፡ ነው ። የመጀመሪያውን ፡ አበባ ፡ እንዳሳያችሁን ፡ ወደ ፊት ፡ የሠራችሁትን ፡ ፍሬ ፡ ለማየት ፡ እንድንችል ፡ ትምህርታችሁን ፡ በትጋት ፡ እንድትቀጥሉ ፡ አደራ ፡ እንላችኋለን ።

# 493

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሰኔ ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከጧቱ ፡ በ፫ ፡ ሰዓት ፡ ጂማ ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ጽሕፈት ፡ቤት ፡ ተገኝተውና ባለጉዳዮችን፡ እየተቀበሉ ፡ ሲያነጋግሩ ፡ ሳሉ ፡ በከፋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የሚገኙ ፡ ነጋዴዎች ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ የተናገሩት ፡ የደስታ ፡ መግለጫ ፡ ቃልና ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የነጋዴዎቹ ፡ ንግግር ።

ግ ር ማ ዊ ፡ ሆ ይ ።

እኛ ፡ በከፋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የምንገኝ ፡ ነጋዴዎች ፡ የገናናው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፳፫ኛ ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓልን ፡ ክብር ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ እስከ ፡ ሰኔ ፡ ወር ፡ መጀመሪያ ፡ ድረስ ፡ $46 005 ፡ አርባ ፡ ስድ ስት ፡ ሺ.ህ ፡ አምስት ፡ የኢ.ትዮጵያ ፡ ብር ፡ አዘጋጅተናል ።

ይህን ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ለበጎ ፡ አድራጎት ፡ የሚያዝበትን ፡ ገንዘብ ፡ ለማበርከት ፡ ጊዜውን ፡ ስንጠባበቅ ፡ ዛሬ ፡ በልዩ ፡ ምክንያት ፡ ጂማ ፡ ስለተ ገኙልን ፡ ገንዘቡን ፡ ለማበርከት ፡ ያጋጠመንን ፡ ዕድል ፡ ልናሳልፍ ፡ አንፈ ቅድምና ፡ ታማኝ ፡ ባሮችዎ ፡ ዛሬ ፡ በዙፋንዎ ፡ ፊት ፡ ቀርበን ፡ ገንዘቡን ፡ እንዲቀበሉን ፡ ከዙፋንዎ ፡ ፊት ፡ ቆመን ፡ እንለምናለን ።

ይህም ፡ አገልግሎታችን ፡ ለተወዳጅ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችንና ፡ ለኢ.ት ዮጵያ ፡ ወደፊት ፡ የማያቋርጥ ፡ መሆኑን ፡ እናረጋግጣለን ።

ለግርማዊነትዎና ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፤
ረጅም ፡ ዕድሜ ፡ እንመኛለን ።
ባሮችዎ ።
በከፋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የምንገኝ ፡ ነጋዴዎች ።

* * *

ለ) ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

በማሰባችሁ ፡ እናመሰግናችኋለን ። ይህንንም ፡ ለእኛ ፡ እርዳታ ፡ ለመ ስጠት ፡ ያደረጋችሁትን ፡ ስጦታ ፡ በዚሁ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ከተማ ፡ ለሚ ገኘው ፡ ሆስፒ.ታል ፡ ማደሻ ፡ እንዲሆን ፡ ፈቅደናል ።

---

# 494

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሰኔ ፡ ፲፫ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፫ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ጂማ፡ የቀዳማዊ ፡ኃይለ ፡ሥላሴን ፡ የሴቶች ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ጐበኙ ። ከዚያም ፡ ቀጥሎ ፡ ወደ ፡ ሚያዝያ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሄደው ፡ የትምህርት ፡ ቤቱን ፡ እርምጃ ፡ ከጐበኙ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ተማሪ ፡ በራሱና ፡ በጓደኞቹ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ ንግግር ፡ አደረገ ። ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትም ፡ በተማሪዎቹ ፡ ሕሊና ፡ ተቀርጾ ፡ የሚኖር ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ ተናገሩ ።



ሀ) የተማሪው ፡ ንግግር ።

ግ ር ማ ዊ ፡ ሆይ ።

በትምህርት ፡ ቤት ፡ ጓደኞቼ ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ እንኳን ፡ ደኅና ፡ የመጡ ልን ፡ እያልኩ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ አጭር ፡ ንግግር ፡ እንዳደርግ ፡ በፍርሃት፡ የግርማዊነትዎን ፡ ፈቃድ ፡ እለምናለሁ ።

ግ ር ማ ዊ ፡ ጃ ን ሆ ይ ።

በመናገሻ ፡ ከተማዎ ፡ ሆነው ፡ ሕዝብዎ ፡ የሚበለጽግበትንና ፡ የኑ ሮው ፡ ሁኔታ ፡ የሚሻሻልበትን ፡ ዘዴ ፡ በማሰብ ፡ ሌት ፡ ከቀን ፡ ያለማረፍ ፡ የሚሠሩት ፡ የማይበቃ ፡ መስሎ ፡ ስለታየዎ ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ ሠለ ጠኑት ፡ የወዳጅ ፡ አገሮች ፡ በመሄድ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ኑሮ ፡ ማሻሻያ ፡ የሚሆኑ ፡ ነገሮች ፡ የሚሠሩበትን ፡ ቦታዎች ፡ እስከ ፡ ፋብሪካ ቸው ፡ ድረስ ፡ ሄደው ፡ በመጐብኘትዎ ፡ ታላቅ ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ ከማግ ኘታችን ፡ በላይ ፡ ለነገው ፡ ሕይወታችን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጽኑ ፡ ተስፋ ፡ አስጨ ብጦናል ።

ይህም ፡ መጐብኘት ፡ ለተድላና ፡ ለደስታ ፡ የተደረገ ፡ ሳይሆን ፡ የሕዝ ብዎ ፡ የኑሮ ፡ ዕድገት ፡ በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ የሚዳብርበትን ፡ ከፍተኛ ፡ ዘዴ፡ ለማምጣት ፡ መሆኑን ፡ ያላወቀው ፡ ኢ.ትዮጵያዊ ፡ የለም ። ግርማዊነትዎን፡ የመሰለ ፡ ታላቅ ፡ መሪ ፡ በአለንበት ፡ ዘመን ፡ ስላጋጠመን ፡ በኛ ፡ በወጣ ቶችዎና ፡ በመላው ፡ ኢ.ትዮጵያ ፡ የማይቀና ፡ ፍጥረት ፡ የሚገኝ ፡ አይመስ ለኝም ።

የወዳጅ ፡ አገሮችን ፡ ጐብኝተው ፡ ከተመለሱ ፡ ወዲህ ፡ የመጐብኘ ትን ፡ ዕድል ፡ ካገኙት ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ሁለተኛነትን ፡ ያገኘነው ፡ እኛ፡ መሆናችንን ፡ ስናስብ ፤ ስሜታችን ፡ በደስታ ፡ ይዋጣል ። ከአራት ፡ ዓመት፡ በፊት ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በጐበኙን ፡ ጊዜ ፡ በልባችን ፡ ተቀርጾ ፡ የሚኖረው፡ «ይህንን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ፉከራችሁን ፡ ሰማን ፤ ይህም ፡ ፉከራችሁ ፡ ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ጠብቆ ፡ ከፍጻሜ ፡ ማድረስ ፡ ያስፈልገዋል ፤ ይህንንም ፡ ስን ላችሁ ፡ መተባበርን ፡ ይዛችሁ ፡ የወገን ፡ አገልጋይ ፡ መሆንን ፡ እንድትፈጽ ሙበት ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ስትፈጽሙ ፡ የግል ፡ ጥቅም ፡ የሚባለውን ፡

ከራሳችሁ ፡ አስወግዳችሁ ፡ ነው ፡ » በሚል ፡ አርእስት ፡ አስፋፍቶ ፡ ከሰጠን ፡ ንጉሣዊ ፡ ምክር ፡ በላይ ፡ ያደረጉልን ፡ የልብስ ፡ ችሮታ ፡ ዘወትር ፡ ከሚደረግልን ፡ ልግሥና ፡ ጋር ፡ ተወዳዳሪ ፡ በመሆኑ ፡ ከትውልድ ፡ እስከ ፡ ትውልድ ፡ የማንረሳው ፡ ነው ።

ይህ ፡ የዛሬው ፡ መጐብኘትዎም ፡ የመላው ፡ ሕዝብዎ ፡ እድገት ፡ የሚሻሻልበትን ፡ ምክርና ፡ ጥናት ፡ በመለገስ ፡ ሠራተኛ ፡ የሆነውን ፡ ሕዝብዎንና ፡ እኛንም ፡ በትምህርት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ የምንገኝ ፡ ወጣቶችዎን ፡ ለማበረታታት ፡ መሆኑን ፡ አውቀነዋል ።

ይህንን ፡ ከፍተኛ ፡ ዕድል ፡ እንድናገኝ ፡ የሚጥሩልንን ፡ ግርማዊነትዎን ፡ የመሰለ ፡ መሪ ፡ ለሰጠን ፡ የነገሥታት ፡ ንጉሥ ፤ የደካሞች ፡ ጋሻ ፡ የሆነው ፡ አምላክ ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ፡ ከማለት ፡ በስተቀር ፡ የሚጨመር፡ ሐተታ ፡ የለም ።

ግርማዊነትዎን ፡ ከልዑላን ፡ ቤተ ፡ ሰቡ ፡ ጋር ፡
አቆይቶ ፡ የዘሩትን ፡ ዘር ፡ ፍሬውን ፡ ለማየት ፡
ያብቃልን ።
ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ፤
ዕድሜ ፡ ለልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡
ወሰን ፤
ዕድሜ ፡ ለልዑላን ፡ ንጉሣዊያን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፤
ኢትዮጵያ ፡ በነፃነቷ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

❊ ❊ ❊

ለ) ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ።

በየጊዜው ፡ አንዳንድ ፡ የምክር ፡ ቃል ፡ ስንሰጣችሁ ፡ ይከብዳችሁ ፡ ይሆናል ፤ ይህ ፡ የሕፃንነት ፡ ወራት ፡ አልፎ ፡ በትምህርት ፡ እየተራመዳችሁ ፡ ስትሄዱ ፡ ግን ፤ ለጊዜው ፡ ከባድ ፡ መስሎ ፡ የታያችሁ ፡ ወደፊት ፡ ለሥራችሁ ፡ ሁሉ ፡ መሪ ፡ ይሆንላችኋል ። ይህን ፡ የሚጠበቀውን ፡ እድገት፡ እኛም ፡ ባንደርስበት ፡ እንኳ ፤ ተከታዮቻችን ፡ ይደርሱበታል ። ስለዚህ ፡ እናንተ ፡ ወጣቶች ፡ በአእምሮ ፤ በትምህርት ፡ ጠንክራችሁ ፡ በሥራችሁ ፡



አገራችሁ ፡ የምትገለገልበትን ፡ ሥራ ፡ ለማከናወን ፡ እንድትችሉ ፡ ስናስብ ፤ እናንተም ፡ የተጣለባችሁን ፡ ኃላፊነት ፡ ከባድ ፡ መሆኑን ፡ ማስታወስ ፡ አለባችሁ ።

አሁን ፡ በተናገራችሁት ፡ ቃል ፡ እንደገለጣችሁት ፡ አሜሪካንና ፡ አውሮፓን ፡ ስንጐበኝ ፡ በተደረገልን ፡ የክብር ፡ አቀባበል ፤ በተመለከትነውም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ተግባር ፡ ተደስተናል ። ይህም ፡ የክብር ፡ አቀባበል ፡ ለእኛ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ላገራችን ፡ ታላቅ ፡ ክብርና ፡ መታወቅ ፡ ምኞታችን ፡ በመፈጸሙ ፡ ነው ። በዘመናዊ ፡ ጥበብ ፡ የተከናወኑትን ፡ ታላላቅ ፡ ሥራዎችና ፡ ፋብሪካዎች ፡ ስንጐበኝ ፡ ከሁሉ ፡ አብልጠን ፡ የተመለከትነው ፤ የሕዝብ ፡ ኑሮ ፡ ምቾት ፡ እየተሻሻለ ፡ የሚሄድበትን ፤ አገር ፡ የሚለማበትንና ፡ የሚበለጽግበትን ፤ ጠላት ፡ የሚያፍርበትን ፤ የሕዝብ ፡ ጤና ፡ የሚጠበቅበትን ፤ በትምህርት ፡ ከሚገኘው ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ ውጤት ፡ መሆኑን ፡ ነው ። ከትምህርት ፡ ሐኪሞች ፡ ይወለዳሉ ፤ አዋቂዎች ፡ ይገኛሉ ፤ መምህራኖች ፡ ይበረክታሉ ። ያልተማሩትን ፡ ለማስተማር ፤ ያላወቁትን ፡ ለማሳወቅ ፡ ይጣጣራሉ ። እኛም ፡ እዚህ ፡ ለመድረስ ፡ በገንዘባችን ፡ እየቀጠርን ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ያስመጣናቸው ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕውቀት ፡ መምህራኖች ፡ በብዙ ፡ ይገኛሉ ።

ይህንንም ፡ ማስታወሳችን ፤ ተምሮ ፡ ማስተማር ፡ ስለሚገባ ፤ በትምህርት ፡ በርትታችሁ ፡ በዕውቀት ፡ ጐልምሳችሁ ፡ ወገናችሁን ፡ በትምህርት ፡ እንድትረዱ ፡ ነው ። በዕውቀት ፡ የገፉችሁ ፤ በትምህርት ፡ የሠለጠናችሁ ፡ እንደሆነ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሳትወሰኑ ፡ ለውጭ ፡ አገርም ፡ ወደኋላ ፡ ለቀሩ ፡ ትተርፋላችሁ ።

ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ አገራችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ምንም ፡ የማይጐድላት ፡ ሆና ፡ ሳለች ፡ የሕዝቧ ፡ ቍጥር ፡ ያነሰ ፡ ነው ። ይህም ፡ ሊሆን ፡ የቻለው ፡ አብዛኛው ፡ በጤና ፡ ጉድለት ፡ ነው ። ከላይ ፡ እንዳስታወስነው ፡ የሕዝብ ፡ ጤና ፡ አጠባበቅም ፡ ሐኪም ፡ የሚገኘው ፡ ከትምህርትና ፡ ከጥበብ ፡ በመወለድ ፡ ነው ። የተናገርናቸውን ፡ ቃሎች ፡ ሰምታችሁ ፡ ላገር ፡ ውለታ ፡ ከፋዮች ፡ ለመሆን ፡ እንድትበቁ ፡ በመላው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ተማሪዎች፡ ተስፋ ፡ ጥለንባችኋል ። ውለታ ፡ ከፋዮች ፡ እንድትሆኑ ፡ ብለን ፡ የምንነግራችሁም ፡ ወገናችሁን ፡ እንድትረዱና ፡ የማታልፈውን ፡ ኢትዮጵያን ፡

እንድታገለግሉ ፡ ነው ።

ቅድም ፡ የምንሰጣችሁ ፡ አንዳንድ ፡ ምክር ፡ ይከብድባችሁ ፡ ይሆ ናል ፡ ያልነው ፡ ስለ ፡ አገራችሁ ፡ ያለባችሁ ፡ ኃላፊነትና ፡ ዕዳ ፡ ከባድ ፡ መሆኑን ፡ በመገመት ፡ ነው ። የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ይደርባችሁ ።

---

# 495

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አፄ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጅማን ፡ በመጐብኘት ፡ ሰኔ ፡ ፲፬ና፡ ፲፭ ፡ ሁለቱን ፡ ቀኖች ፡ ካሳለፉ ፡ በኋላ ፡ ሰኔ ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፫ ፡ ሰዓት ፡ በልዩ ፡ አውቶ ሞቢል ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ተመለሱ ። ከመመለሳቸውም ፡ በፊት ፡ ሰኔ ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ በአገሩ ፡ ሕዝብና ፡ በመንግሥት ፡ እርዳታ ፡ የተቋቋመውን ፡ የእስላም ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሰኔ ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ሲጐበኙ ፡ ከተማሪዎቹ ፡ መካከል ፡ ሁለት ፡ ተማሪዎች ፡ የተናገሩትና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ ምክር ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

ሀ) ከተማሪዎቹ ፡ አንደኛው ፡ የተናገረው ፡ ቃል ።

የ ኢ ት ዮ ጵ ያ ፡ ብ ር ሃ ን ፡

ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ።

በአስተማሪዎቼና ፡ በጓደኞቼ ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ንግግሬን ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ፊት ፡ ቀርቤ ፡ እገልጻለሁ ። ከዚህም ፡ ቀደም ፡ የከፋን ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ለመጎብኘት ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ እዚሁ ፡ ትምህ ርት ፡ ቤታችን ፡ ድረስ ፡ መጥተው ፡ የምንማርበትን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መርቀውልን ፡ እኛም ፡ በተወለድንበት ፡ አገር ፡ ከአባት ፡ እናታችን ፡ ጋር ፡ ሆነን ፡ የሃይማኖታችንን ፡ ትምህርት ፡ ተግተን ፡ እንድንማርና ፡ እንዲሁም ፡ አስተማሪ ፡ ቀጥረውልን ፡ ሌላውን ፡ ትምህርት ፡ አማርኛንና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ በየዐይነቱ ፡ ተምረን ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ከፈጸምን ፡ በኋላ ፡ አገራችንንና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችንን ፡ ነፃነታችንን ፡ እንድናኮራና ፡ በሥል ጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ደርሰን ፡ ለማለፍ ፡ እንድንችል ፡ በየመጻሕፍቱና ፡ በቃልዎም፡ ጭምር ፡ የመከሩንን ፡ መልካሙን ፡ ምክርዎን ፡ በመከተል ፡ ትምህርታች ንን ፡ በሰፊው ፡ በማጥናት ፡ ላይ ፡ ነን ።



ግርማዊነትዎ ፡ ከሁሉ ፡ ሥራም ፡ አስቀድመው ፡ ትምህርትን ፡ ለሚ ናፍቁ ፡ ሕዝቦችዎ ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ በየአውራጃው ፡ እንዲሁም ፡ በየ ወረዳዎችና ፡ በምክትል ፡ ወረዳዎች ፡ ገና ፡ ለሚወለዱት ፡ ቡቃያዎች ፡ ከመወለዳቸው ፡ በፊት ፡ በትምህርት ፡ እንዲጐለምሱ ፡ ትንሽና ፡ ትልቅ ፡ ጌታና ፡ ድሃ ፡ ሳይባባሉ ፡ ዕውቀትን ፡ ገብይተው ፡ በትምህርት ፡ ያገኙትን፡ ደረጃ ፡ እንዲይዙ ፡ አስበው ፡ የዘለዓለም ፡ ሐውልት ፡ ለተከሉልን ፡ ዋጋ ዎን ፡ ቸርነቱ ፡ የማያልቅበት ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜዎን ፡ እንዲያረዝምልን ፡ እየለመን ፡ የልጅ ፡ ልጅዎ ፡ ዘርና ፡ ዕድሜ፡ እንዲቆይልን ፡ ጸሎታችንን ፡ ወደ ፡ አምላካችን ፡ እናደርሳለን ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ፤
ዕድሜ ፡ ለልዑላን ፡ ቤተ ፡ ሰቦችዎ ፤
ኢትዮጵያ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

* * *

ለ) ከተማሪዎቹ ፡ ሁለተኛው ፡ የተናገረው ፡ ቃል ።

የ ኢ ት ዮ ጵ ያ ፡ ብ ር ሃ ን ፡

ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ።

በአስተማሪዎቼና ፡ በጓደኞቼ ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ይህንን ፡ ትምህርት ፡ ቤታችንን ፡ በመጐብኘትዎ ፡ ዕድለኛ ፡ መሆናችን ፡ ተሰምቶን፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ምስጋናችንን ፡ እናቀርባለን ።

ግ ር ማ ዊ ፡ ሆ ይ ።

የግርማዊነትዎ ፡ ተክል ፡ መሆናችን ፡ ዘለዓለም ፡ የማይዘነጋ ፡ ነው ። አገሬ ፡ ከጨለማ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ እንድትወጣ ፡ በማለት ፡ የብርሃን ፡ ጮራ፡ በእጅዎ ፡ ጨብጠው ፡ ለመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የዘሩት ፡ ለእኛም ፡ ደርሶን ፡ ብርሃኑ ፡ በርቶልን ፡ ዘለዓለም ፡ በማይረሳ ፡ ታሪክ ፡ ግንባር ፡ ላይ ፡ በወርቅ ፡ ፊደል ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ። የተመኙልንንም ፡ ነገሮች ፡ ለመፈ ጸም ፡ ብለን ፡ መትጋታችንን ፡ አላቋረጥንም ። የአላህ ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ ለአ ገራችንና ፡ ለመንግሥታችን ፡ መልካም ፡ ወታደሮች ፡ ሆነን ፡ ለመገኘትና፡

በጠረጉልን ፡ መንገድ ፡ እንድንራመድ ፡ ያብቃን ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ፤
ዕድሜ ፡ ለልዑላን ፡ ቤተ ፡ ሰቦችዎ ፤
ኢትዮጵያ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

❊ ❊ ❊

ሐ) ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ ምክር ።

ትምህርት ፡ ላገር ፡ ፋና ፡ ነው ፤ በጭለማ ፡ ከመሄድ ፡ በብርሃን ፡ መሄድ ፡ የበለጠ ፡ ነው ፤ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በየቦታው ፡ እንዲከፈት ፡ ያደረግ ግነው ፡ አንድነትን ፡ አጽንታችሁ ፡ ሳትለያዩ ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሆናችሁ ፡ እንድትማሩ ፡ ነው ።

በርትታችሁ ፡ ተማሩ ፤ ከተማራችሁ ፡ ዋጋችሁን ፡ አታጡም ። ትምህርት ፡ ከመለያየት ፡ የሚያድንና ፡ አንድ ፡ የሚያደርግ ፡ ታላቅ ፡ መሣሪያ ፡ መሆኑን ፡ አትዘንጉ ።

---

# 496

የኢትዮጵያ ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፤ የተመሠረተበትን ፡ የኻያኛውን ፡ ዓመት ፡ መታሰቢያ ፡ በዓል ፡ ለማክበርና ፡ ትምህርታቸውን ፡ ለጨረሱት ፡ ለዘጠኝ ፡ ነርሶች ፡ ዲፕሎማ ፡ ለመስጠት፡ ሐምሌ ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ዩኒቤርስቲ ፡ ኮሌጅ ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ ባደረገው ፡ ሥነ በዓል ፡ ላይ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ተገኝተውና ፡ ዲፕሎማውን ፡ ሲሰጡ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ።

ሀ) የቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፡ ም/ፕሬዚዳንት ፡ የክቡር ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ተፈራ ፡ ወርቅ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፤
ግርማዊት ፡ እቴጌ ፤
ልዑላን ፡ መሳፍንት ፤
ክቡራን ፡ እንግዶች ፤

በግርማዊነትዎና ፡ በግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጠባቂነት ፡ የሚካሄደው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፡ የተመሠረተበትን ፡ ኻያ



ኛውን ፡ ዓመት ፡ በዓል ፡ በምናከብርበት ፡ በዛሬ ፡ ቀን ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ የግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ በመካከላችን ፡ ስለተገኛችሁልን ፡ በቦርዱ ፡ አባሎችና ፡ በራሴም ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋናችንን ፡ እንዳቀርብ ፡ እንዲፈቀድልኝ ፡ እለምናለሁ ። እንደዚሁም ፡ ባለፈውም ፡ ሆነ ፡ ባሁኑም ፡ ጊዜ ፡ የማኅበሩ ፡ ረዳት ፡ የሆኑት ፡ እንግዶቻችን ፡ ዛሬ ፡ የበዓላችን ፡ ተካፋይ ፡ በመሆን ፡ ስለ ፡ ተገኙልን ፡ የቦርዱን ፡ አባሎች ፡ የደስታ ፡ ጥልቅ ፡ ስሜት ፡ ልገልጥ ፡ እወዳለሁ ።

ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ ከግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ በየጊዜው ፡ ያገኘው ፡ እርዳታና ፡ መልካም ፡ አርአያ ፡ የማኅበሩን ፡ ሥራ ፡ ለማነቃቃት ፡ ታላቅ ፡ እርዳታና ፡ ድጋፍ ፡ ይሆናል ። የሌሎቹም ፡ ረዳቶቻችን ፡ ደግነትና፡ ኅብረት ፡ አስቸጋሪ ፡ ከሆኑት ፡ ጊዜያቶች ፡ እያለፍን ፡ ወደ ፡ ተሻሻለና ፡ ወደተመቸ ፡ ሁኔታ ፡ እንድናልፍ ፡ ረድቶናል ።

የኢትዮጵያ ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፡ ኻያኛ ፡ ዓመት ፡ በሚከበርበት ፡ በሁላችን ፡ ዘንድ ፡ ሊታወስ ፡ በሚገባው ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ የማኅበሩ ፡ መስፋፋትና ፡ እድገት ፡ ባጭሩ ፡ ባስረዳ ፡ ከቦታው ፡ የወጣ ፡ ነገር ፡ እንደማይሆን ፡ አምናለሁ ።

የኢትዮጵያ ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፡ ከ፪ኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ በፊት ፡ ኢትዮጵያ ፡ በችግር ፡ አፋፍ ፡ በነበረችበት ፡ ጊዜ ፡ ተወጥኖ ፡ ሐምሌ ፡ ፩ ፡ ፲፱፻፳፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በተነገረ ፡ ንጉሣዊ ፡ አዋጅ ፡ ተመሠረተ ። በዚያው ፡ ዓመት ፡ የተወለደው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፡ ከ፲፱፻፳፯ ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ. ም. ፡በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ በተደረገው ፡ የግፍ ጦርነት ፡ ሥርዓተ ፡ ጥምቀቱን ፡ በእሳት ፡ ነበልባል ፡ የፈጸመው ፡ ከሌሎች፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ አምቡላንስ ፡ ሠራዊት ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አገልግሎት ፡ አድርጓል ።

የኢትዮጵያ ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፡ የችግር ፡ ድምጹን ፡ በማሰማት ፡ ለእርዳታ ፡ የደረሱለት ፡ ሐኪሞችና ፡ የሕክምና ፡ መሣርያዎች ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ቢመጡም ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ የሚሆኑ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በዚሁ ፡ አምቡላንስ ፡ ሠራዊት ፡ ውስጥ ፡ ልኮ ፡ የተቀደሰ ፡ ተግባራቸውን ፡ በመፈጸም ፡ ሕይወታቸውን ፡ የሠውት ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። ለእርዳታ ፡ መጥተው ፡ ከነበሩት ፡ ሐኪሞች ፡ አንዳንዶቹ ፡ አሁንም ፡ በንጉሠ ፡ ነገ

ሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ መገኘታቸውን ፡ ስንገልጽ ፡ ደስ ፡ ይለኛል።

የቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፡ ከብዙ ፡ በጎ ፡ አድራጊ ፡ ወዳጆች ፡ ጋር ፡ በመረዳዳት ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ለቈሰሉት ፡ የቊስል ፡ ማሠሪያ ፡ ጨርቆች ፡ ንና ፡ የቊበለኛ ፡ ማጓዣ ፡ ቃሬዛዎችን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ላይ ፡ እያደራጀ ፡ ስንቅ ፡ ጨምሮ ፡ ይልክ ፡ ነበር ። በዚያው ፡ ዘመን ፡ በጥቂቶች ፡ የኢትዮጵ ያ ፡ ወይዛዝር ፡ ተቋቁሞ ፡ የነበረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሴቶች ፡ ሥራ ፡ ማኅ በር ፡ ያለድካምና ፡ ያለመሰልቸት ፡ ለቊስለኞች ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር፡ በማደራጀትና ፡ ቊስለኞችንም ፡ በመርዳት ፡ የፈጸመውን ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ ሳላስታውስ ፡ አላልፍም ። ከልዩ ፡ ልዩ ፡ የዓለም ፡ ክፍሎች ፡ ከተላኩት ፡ የገንዘብና ፡ የመድኃኒት ፡ እርዳታዎች ፡ በላይ ፡ ከታላቂቱ ፡ ብሪታንያ ፡ ከግብጽ ፡ ከፊላንድና ፡ ከሆላን ፡ ከኖርዊይና ፡ ከስዊድን ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ መሣርያ ፡ አምቡላንሶችና ፡ ሐኪሞች ፡ ደረሱለት ። ይህም ፡ ከርሱ ፡ የሚጠበቀውን ፡ ተግባር ፡ በመጠኑ ፡ ለመፈጸም ፡ አስቻለው ። ያ ፡ ሁሉ ፡ የጭንቀት ፡ ማዕበል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ አልፎ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነፃ ነቷን ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አገኘች ።

የኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡ እንደተረጋገጠ ፡ መልካም ፡ መታሰቢያቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ሕያው ፡ ሆኖ ፡ የሚኖረውና ፡ በስማቸው ፡ የሚጠራ ፡ ሆስፒታል ፡ የቆመላቸው ፡ ልዕልት ፡ ፀሐይ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የቀይ ፡ መስቀልን ፡ ማኅበር ፡ መልሶ ፡ ለማቋቋምና ፡ ሥራውን ፡ በማደስ ፡ ለመርዳት ፡ የእንግሊዝ ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ ሠራተኞችን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ እናት ፡ አገራቸው ፡ መጥተው ፡ የተቻላቸውን ፡ ሁሉ ፡ ማድረጋቸውን ፡ ማንም ፡ አይዘነጋውም ።

የኢትዮጵያ ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ሳይ ሆን ፡ በሰላምም ፡ ጊዜ ፡ አገልግሎቱን ፡ መስጠት ፡ ተግባሩ ፡ መሆኑን ፡ በመረዳት ፡ ለዚህ ፡ ሥራ ፡ በክቡር ፡ አቶ ፡ አበበ ፡ ረታ ፡ ሰብሳቢነት ፡ አንድ ፡ ኮሚቴ ፡ እንዲቆም ፡ ተደርጎ ፡ የሰላም ፡ ጊዜ ፡ ሥራውን ፡ ፕሮግ ራም ፡ አቋቋመ ። በጥር ፡ ወር ፡ ፲፱፻፵ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የመጀመሪያው ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባዔ ፡ ተደርጎ ፡ ልዑል ፡ መርዕድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ የማ ኅበሩን ፡ ፕሬዚዴንትነት ፡ ተቀበሉ ። መጀመሪያው ፡ አዋጅ ፡ ተሻሽሎ ፡



በጥቅምት ፡ ወር ፡ ፲፱፻፵፱፡ ዓ. ም. ፡በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ በ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፡ ከሌሎች ፡ አገ ሮች ፡ ማኅበሮችና ፡ ጀኔቭ ፡ ላይ ፡ በሚገኘው ፡ ጠቅላላ ፡ የዓለም ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ የሚገባውን ፡ ቦታ ፡ ያዘ ።

ማኅበራችን ፡ በሰላም ፡ ጊዜ ፡ ከሚፈጽማቸው ፡ ተግባሮች ፡ ያስገኛ ቸው ፡ የሥራ ፡ ፍሬዎች ፡ አንዱ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መልካም ፡ ፈቃድና ፡ ችሮታ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሆስፒታል ፡ ቅጥር ፡ ውስጥ ፡ የቆመው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የመጀመሪያው ፡ የነርሶች ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የመጀመሪያዎ ቹን ፡ ነርሶች ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሆስፒታሎች ፡ ለማበርከት ፡ ችሏል ። አንዳን ዶቹም ፡ እስከ ፡ ኮሪያ ፡ ድረስ ፡ ሄደው ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ለአገራቸው ፡ አገ ልግለዋል ። ዛሬ ፡ በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ከሚገኙት ፡ ፳፫ ፡ ተማሪዎች ፡ ዘጠኙ ፡ የምስክር ፡ ወረቀታቸውን ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ እጅ ፡ ይቀበላሉ ።

ማኅበሩ ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ ያቋቋመው ፡ የአምቡላንስ ፡ አገ ልግሎት ፡ ሕመምተኞቹን ፡ በነፃ ፡ በማመላለስ ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ሰዓት ፡ ሙሉ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ይሠራል ።

በ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተቋቋመው ፡ የማኅበሩ ፡ የስፌት ፡ ሥራ ፡ ክፍል፡ ከአሜሪካ ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ የተሰጡትን ፡ የስፌት ፡ መኪናዎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በማዋል ፡ ቊጥራቸው ፡ እያደገ ፡ በሚሄደው ፡ የብዙ ፡ አገር ፡ ተወላጆች ፡ በመልካም ፡ ይከናወናል ። ከዚሁ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ የሚገኘው ፡ የስፌት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አሥር ፡ ተማሪዎች ፡ የስድስት ፡ ወር ፡ ትም ርት ፡ ጨርሰው ፡ ስምንቱ ፡ የምስክር ፡ ወረቀታቸውን ፡ ይቀበላሉ ።

በማኅበራዊ ፡ ተግባር ፡ ረገድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅ በር ፡ የሚፈጽማቸው ፡ አገልግሎቶች ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ የደረሱበትን ፡ ያልታወቀውን ፡ ሰዎች ፡ መፈለግ ፡ ድሆች ፡ በሆስፒታል ፡ በነፃ ፡ እንዲታ ከሙ ፡ ማድረግ ፡ ዓይናቸው ፡ ለደከመ ፡ ድሆች ፡ መነጽር ፡ በነፃ ፡ መስ ጠት ፡ ነው ። መጀመሪያ ፡ የተጠቀሰው ፡ አገልግሎት ፡ በሰላም ፡ ጊዜ ፡ ባለመፈለጉ ፡ በዚያ ፡ ፈንታ ፡ ማኅበሩ ፡ የቀጠራቸው ፡ አስተማሪዎችና ፡ ነርሶች ፡ በሚያስፈልገው ፡ ቦታ ፡ እየሄዱ ፡ እርዳታቸውን ፡ ያደርጋሉ ። ለምሳሌ ፡ ወደ ፡ ልዕልት ፡ ዘነበ ፡ ወርቅ ፡ የደዌ ፡ ሥጋ ፡ ሆስፒታል ፡ እየ

ሄዱ ፡ በዚያው ፡ ከሚገኙት ፡ ሕሙማን ፡ መካከል ፡ የአስታማሚነትና ፡ የመጀመሪያውን ፡ የሕክምና ፡ እርዳታ ፡ የሚያደርጉ ፡ ሰዎችን ፡ ያሠለጥናሉ ።

በዘንድሮው ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ አዳዲስ ፡ ሥራዎችን ፡ አቋቁሚል ፤ አንደኛ ፡ ለማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ የጽዳት ፡ ኢንስፔክተሮችና ፡ በግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለሚገኙ ፡ ወጣቶች ፡ የመጀመሪያውን ፡ የሕክምና ፡ እርዳታ ፡ የምታስተምር ፡ አዋቂ ፡ ቀጥሮ ፡ ያስተማራቸው ፡ ዛሬ ፡ ዲፕሎማቸውን ፡ ለመቀበል ፡ ቀርበዋል ።

ሁለተኛ ፡ በግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ትምህርተ ፡ ቤት ፡ የመጀመሪያ ፡ ሕክምና ፡ እርዳታ ፡ ማድረግና ፡ የቤት ፡ ነርስነት ፡ ትምህርት ፡ የሚሰጥበት ፡ የወጣቶች ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፡ አቋቁሚል ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ በየትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የሚገኙት ፡ ልጆች ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ተማሪዎች ፡ ጋር ፡ እንዲጻጻፉና ፡ ጠቃሚ ፡ ነገሮችን ፡ እንዲለዋወጡ ፡ ማድረግ ፡ ጀምሮአል ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሊፈጸም ፡ የቻለውና ፡ ማኅበራችንም ፡ አሁን ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ በጃንሆይ ፡ ሜዳ ፡ ያደረገው ፡ የቀይ ፡ መስቀል ፡ በዓል ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲያገኝ ፡ ረዳት ፡ የሆነው ፡ ያጋገርዎቻችንና ፡ በበጎ ፡ ፈቃዳቸው ፡ የረዱን ፡ ሰዎች ፡ ድጋፍ ፡ ስለሆነ ፡ በማኅበሩ ፡ ስም ፡ አመሰግናቸዋለሁ ።

ከላይ ፡ የተጠቀሱትም ፡ የማኅበሩ ፡ ሥራዎች ፡ ለሚመጣውም ፡ ዓመት፡ በሙሉ ፡ እንደሚቀጥሉ ፡ ስገልጽ ፡ ደስ ፡ እያለኝ ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፡ ከተመሠረተበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ የኻያኛውን ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ እስከሚከበርባት ፡ እስከ ፡ ዛሬይቱ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ የግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ሰፊ ፡ እርዳታና ፡ በጎ ፡ አስተያየት ፡ ስለአልተለየው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋናውን ፡ እንዲያቀርብ ፡ እንዲፈቀድለት ፡ ዝቅ ፡ ብዬ ፡ እለምናለሁ ።

ክቡራን ፡ መኳንንትና ፡ ወይዛዝር ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ሆነ ፡ ላጭር ፡ ማኅበሩን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጉዳይ ፡ በመርዳት ፡ ለፈጸማችኋቸው ፡ ብዙ ፡ አገልግሎቶች ፡ የማኅበሩን ፡ ምስጋና ፡ እያቀረብሁ ፡ በማኅበረተኝነታችሁ ፡ የገንዘብ ፡ እርዳታችሁን ፡ እንደምታደርጉልን ፡ ሁሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡



የምንሰጠውን ፡ መልካም ፡ አሳቢነታችሁንና ፡ የሥራ ፡ እርዳታችሁንም ፡ እንደማትነፍጉን ፡ እንተማመንባችኋለን ።

ፕሬዚዴንታችሁ ፡ ልዑል ፡ መርዕድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ በመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ ዛሬ ፡ ከዚህ ፡ ሊገኙልን ፡ ባይችሉም ፡ ላደረጉልን ፡ ብዙ፡ እርዳታ ፡ ማኅበሩ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ምስጋናውን ፡ ያቀርብላቸዋል

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፤<br>
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፤<br>
ዕድሜ ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፤<br>
ኢትዮጵያ ፡ ለዘለዓለም ፡ በነፃነቷ ፡ ትኑር ።

❊ ❊ ❊

ለ) የማኅበሩ ፡ አባል ፡ ልጅ ፡ ኃይሉ ፡ ደስታ ፡ ካሣ ፡ ስለ ፡ ነርሶቹ ፡ ምክር ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ።

በዚች ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍጥሯት ፡ ሰዎች ፡ አሻሻልናት ፡ በሚሏት ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ከዓላማችሁ ፡ ጋር ፡ ተሰልፋችሁ ፡ ስትታዩ ፡ ለመላዋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የምታኰሩና ፡ የምትረዱ ፡ ከመሆናችሁም ፡ በላይ ፡ ለተሠቃዩ ፡ ሁሉ ፡ ተስፋን ፡ ይዛችኋል ። ከሁሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥራንና ፡ ታላቅ ፡ መሥዋዕትነትን ፡ የሚጠይቀው ፡ «ባልንጀራህን ፡ እንደራስህ ፡ ውደድ ፡ » የሚለው ፡ የተቀደሰ ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ። የዚህንም ፡ የትእዛዝ ፡ ጥሪ ፡ በመቀበላችሁ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተቀበላችሁ ። አስፈላጊውንም ፡ ዝግጅት ፡ ከማግኘታችሁ ፡ ዛሬ ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እጅ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ተቀብላችኋል ። እንግዲህ ፡ የማላችሁትን ፡ መሐላ ፡ ለማክበር ፡ ግዴታ ፡ ገብታችኋልና ፡ ወደፊት ፡ ከጥፋትና ፡ ከጨለማ ፡ ከመከራና ፡ ከሥቃይ ፡ ጋር ፡ ጦርነት ፡ ስትገጥሙ ፡ ትኖራላችሁ ። ለዚህም ፡ በምታደርጉት ፡ ተጋድሎ ፡ በሰላምም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ በዓለም ፡ ተሠራጭተው ፡ በብዙ ፡ ሺህ ፡ የሚቆጠሩ ፡ የጦር ፡ ጓደኞች ፡ አሏችሁ ። ድል ፡ ሰጭአችሁም ፡ የርኅራኄው ፡ ምንጭ ፡ ኃይሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነውና ፡ እምነታችሁን ፡ በእሱው ፡ ብቻ ፡ ከመሠረታችሁት ፡ ማንኛውም ፡ ማዕበል ፡ ቢሆን ፡ ሊነካችሁ ፡ አይችልም ። ደግ ፡ አሳ

ብን ፡ ይዘው ፡ አምላክን ፡ ከሚረሱ ፡ መጥፎ ፡ ሐሳብን ፡ ይዘው ፡ አምላክን ፡ የሚያስታውሱ ፡ የበለጠ ፡ መልካም ፡ ፍጻሜ ፡ ያገኛሉ ። ስለዚህ ፡ ጣፋጭ ፡ ውሆችን ፡ ይዘው ፡ ወደማይጣፍጠው ፡ ውቅያኖስ ፡ እንደሚገቡት ፡ ወንዞች ፡ እንዳትሆኑ ፡ መንገዳችሁን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲያቃናላችሁ ፡ የሁላችንም ፡ የጠለቀ ፡ ምኞት ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ የናንተም ፡ የዘወትር ፡ ጸሎት ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ። ዛሬ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በተገኙበት ፡ በዚህ ፡ በተከበረ ፡ ስብሰባ ፡ መካከል ፡ መልካሙን ፡ የፍሎረንስ ፡ ናይትንጌልን ፡ ፋና ፡ ከግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ እጅ ፡ ተቀብላችሁ ፡ ይህ ፡ የፋና ፡ ብርሃን ፡ እንዳይጠፋባችሁ ፡ ከርኅራኄ ፡ ብዛት ፡ ከሚገኘው ፡ ዘይት፡ መመገብ ፡ ይኖርባችኋልና ፡ እግዚአብሔር ፡ ርኅራኄን ፡ አብዝቶ ፡ ይስጣችሁ ።

* * *

ሐ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መሪ ፡ ቃል ።

የኢትዮጵያ ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፡ የተመሠረተበትን ፡ የ፵ኛውን ፡ ዓመት ፡ በዓል ፡ በሚያከብርበት ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ ለመገኘት ፡ በመቻላችን ፡ ደስ ፡ ብሎናል ።

ማኅበሩ ፡ ባለፉት ፡ ዘመናት ፡ የፈጸማቸው ፡ ሥራዎች ፡ እንደተቃኑለት ፡ ሁሉ ፡ የወደፊት ፡ ሥራዎቹም ፡ እንዲቃኑለት ፡ እንመኝለታለን ። ይህም ፡ ምኞታችን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በችግራችን ፡ ጊዜ ፡ ስንጠራቸው ፡ ለደረሱልን ፡ ለወዳጆቻችን ፡ አገሮች ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበሮች ፡ ጭምር ፡ የተዘረጋ ፡ ነው ። በጦር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ወዳጅና ፡ ጠላት ፡ ሳይል ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ሥቃይ ፡ ከማቃለል ፡ የበለጠ ፡ እውነተኛ ፡ አገልግሎት ፡ ሊኖር ፡ አይችልም ። ስለዚህ ፡ የቀይ ፡ መስቀል ፡ ተግባር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አድናቆት ፡ ሊሰጠው ፡ የተገባ ፡ ነው ።

የቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፡ በኢትዮጵያ ፡ የነርስነት ፡ ትምህርት ፡ እንዲስፋፋ ፡ ለማድረግ ፡ ያለ ፡ አንዳች ፡ ጥቅም ፡ በፈቃዳቸው ፡ በሚሠሩት ፡ አባሎቹ ፡ አማካይነት ፡ ያደረገው ፡ ጥረትና ፡ ድካም ፡ የሚያስመሰግን ፡ ነው ።



ከዚህ ፡ በፊት ፡ የነርስነት ፡ ትምህርታቸውን ፡ ከጨረሱት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ከሚገኙት ፡ እኅቶቻቸው ፡ ጋር ፡ ታላቅ ፡ ተብሎ ፡ ሊቈጠር ፡ የተገባውን ፡ የተከበረ ፡ ተግባር ፡ ለመጀመር ፡ ለተዘጋጁት ፡ ዛሬ ፡ የምስክር ፡ ወረቀታቸውን ፡ ለሚቀበሉት ፡ ወጣቶች ፡ በተለይ ፡ ጥቂት ፡ ቃሎች ፡ እንነግራችኋለን ።

የአስታማሚነት ፡ ሥራ ፡ ቀላል ፡ አይደለም ፡ ባሳለፋችኋቸውም ፡ የትምህርት ፡ ዓመታት ፡ ለዚህ ፡ ትምህርት ፡ ዐይነተኛ ፡ ተግባር ፡ የሆነውን ፡ ሥርዓት ፡ ጠባቂነት ፡ ለመቀበል ፡ በመዘጋጀታችሁ ፡ ከሌሎች ፡ ሴቶች ፡ የተለያችሁ ፡ ሆናችኋል ። ዛሬ ፡ ከተሰጣችሁ ፡ ክብር ፡ ጋር ፡ የተቀበላችሁት ፡ የአላፊነትም ፡ ሸክም ፡ በዚሁ ፡ መጠን ፡ መሆኑን ፡ አትዘንጉት ።

የሚኖርባችሁ ፡ አላፊነት ፡ ምናልባት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከዐቅማችሁ ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ መስሎ ፡ ይታይ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ያለፋችሁትን ፡ ትምህርት ፡ ለመፈጸም ፡ ተቻላችሁ ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ ተካፋይ ፡ የምትሆኑበትን ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ሲያያይዝ ፡ የመጣው ፡ የተከበረ ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ እንደማያቅታችሁ ፡ እርግጥ ፡ ይመስላል ። ለወደፊት ፡ ሕይወታችሁ ፡ መሪ ፡ የሆነውን ፡ ዓላማችሁን ፡ ያገኛችሁባቸውን ፡ በዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ያሳለፋችኋቸውን ፡ የትምህርት ፡ ዘመናት ፡ እንድታስታውሱዋቸው ፡ ያስፈልጋል ። ለትምህርት ፡ ያነቃቃችሁን፡ ካስተማሪዎቻችሁ ፡ ያገኛችሁትን ፡ መልካም ፡ አርአያ ፡ ዘወትር ፡ ጠብቁት ፡ አስቡትም ። ለተጣለባችሁ ፡ አደራ ፡ በቂ ፡ ሆናችሁ ፡ እንድትገኙ ፡ በወጣትነታችሁ ፡ ዘመን ፡ ጠንክራችሁ ፡ ሥሩ ። እስከ ፡ ዘመናችሁ ፡ ፍጻሜ ፡ ያገለግላችኋል ። መልካም ፡ ስም ፡ ቅርስም ፡ ታስቀራላችሁ ።

የትምህርታችሁ ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ በልባችሁ ፡ ርኅራኄን ፡ ማሳደር ፡ ግብዝነትን ፡ መናቅ ፡ ይሁን ። ርኅራኄ ፡ ላንዲት ፡ አስታማሚ ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ገንዘብ ፡ መሆኑን ፡ ዕወቁ ። በራሳችሁ ፡ ላይ ፡ ያደረጋችሁት ፡ ቆብ ፡ ለፈጸማችሁት ፡ ትምህርት ፡ ምልክት ፡ ነው ።

ቆባችሁን ፡ ስታደርጉ ፡ መንፈሳዊ ፡ ኩራት ፡ ይሰማችሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ መልካም ፡ አስታማሚ ፡ የምትሆኑት ፡ ልባችሁ ፡ በርኅራኄ ፡ የተመላ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

በሽተኞችን ፡ ለማጽናናት ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ጭንቀት ፡ ለማቃለልና ፡ ሐኪሙንም ፡ በከባድ ፡ ሥራው ፡ ለመርዳት ፡ እንድትችሉ ፡ ታዛዥና ፡ ርኅ

ሩኅ ፡ መሆንን ፡ ተማሩ ። መታዘዝንና ፡ ግብረ ፡ ገብነትን ፡ ካላወቃችሁ ፡ ያጠናችሁት ፡ ቴክኒክና ፡ የሳይንስ ፡ ዕውቀታችሁ ፡ የደከማችሁበትም፡ ትምህርት ፡ ሁሉ ፡ ስመ ፡ ጥሩዎቹ ፡ የሥራ ፡ ጓደኞቻችሁ ፡ ወደ ፡ ደረሱበት ፡ ደረጃ ፡ ሊያደርሳችሁ ፡ አይችልም ።

እግዚአብሔር ፡ ለሁላችንም ፡ ብርቱ ፡ ሠራተኛና ፡ ርኅሩኅ ፡ አገልጋይ ፡ ለመሆን ፡ እንድንችል ፡ ኃይል ፡ ሰጥቶናል ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ፡ ረገድ፡ ለሴቶች ፡ የሰጣችሁ ፡ ኃይል ፡ ከወንዶች ፡ የበለጠ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ኃይል ፡ ዕለት ፡ በዕለት ፡ በምትፈጽሙት ፡ የአስታማሚነት ፡ ተግባራችሁ ፡ ላይ ፡ አውሉት ። የናንተን ፡ እርዳታና ፡ ማጽናናት ፡ የማይፈልግ፡ በሽተኛ ፡ አይገኝም ። ለበሽተኛ ፡ ጤናችሁ ፡ እያለ ፡ ታማሚውን ፡ ለመምሰል ፡ ታላቅ ፡ ትዕግሥት ፡ ከባድ ፡ ሸክማችሁ ፡ መሆኑን ፡ አትዘንጉ ።

የአስታማሚነት ፡ ትምህርታችሁን ፡ በሚገባ ፡ ስለፈጸማችሁ ፡ ደስ ፡ ብሎናል ። በፈጸማችሁትም ፡ ትምህርት ፡ ልትኮሩ ፡ ይገባችኋል ። ወደፊት፡ የሚከተሉዋችሁ ፡ ነርሶች ፡ በሺ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ናቸው ። በሥራችሁም ፡ እንድትጠቀሙበትና ፡ ደስ ፡ ያላችሁ ፡ እንድትሆኑ ፡ እንመኝላችኋለን ።

---

# 497

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ.ም ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ዩኒቬርስቲ ፡ ኮሌጅ ፡ ተገኝተው ፡ ትምህርታቸውን ፡ ለፈጸሙት ፡ ወጣቶች ፡ የቢ.ኤ.ዲግሪና ፡ ዲፕሎማ ፡ እንዲሁም ፡ ሰርቲፊኬት ፡ ሲሰጡ ፡ የኮሌጅ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ቦርድ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ክቡር ፡ ብላታ ፡ መርስዔ ፡ ኀዘን ፡ ወልደ ፡ ቂርቆስና ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ ዶክተር ፡ ሱዊስ፡ ማት ፡ ከተናገሩ ፡ በኋላ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ።

ሀ) የሊቀ ፡ መንበሩ ፡ የክቡር ፡ ብላታ ፡ መርስዔ ፡ ኀዘን ፡ ወልደ ፡ ቂርቆስ ፡ ንግግር ።

ግ ር ማ ዊ ፡ ሆ ይ ።

የኢትዮጵያ ፡ የትምህርት ፡ እርምጃ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ሠሪነትና ፡ መሪነት ፡ እየተስፋፋ ፡ ከመሄዱ ፡ የተነሣ ፡ የዛሬ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ተመርቆ ፡ የተከፈተው ፡ ይህ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ ኮሌጅ ፡ የዲግሪ ፡ ማዕርግ ፡ መስጠት ፡ ከጀመረ ፡ ዛሬ ፡ ሁለተኛ ፡ ዓመት ፡ ነው ። ከግርማዊነትዎ ፡ በተሰ



ጠው ፡ ንጉሣዊ ፡ ቻርተር ፡ መሠረት ፡ የባለ ፡ ሥልጣኖች ፡ ቦርድ ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ተቋቁሞ ፡ በሥልጣኑ ፡ ሊሠራበት ፡ ጀምሮአል ። የግርማዊነትዎ ፡ እርዳታ ፡ በየጊዜው ፡ ደጋፊያችን ፡ ስለ ፡ ሆነና ፡ የመንግሥቱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ በኅብረት ፡ ሥራ ፡ ስላገዙን ፤ የኮሌጁ ፡ አስተዳደር ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ተከናውኖ ፡ ተገኝቷል ።

የኮሌጁ ፡ ተማሪዎች ፡ ቍጥር ፡ እየበዛና ፡ እያደገ ፡ ሄዶአል ። በዚህም ፡ ዓመት ፡ በሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ (በአርት ) ፋክሊት ፡ ፹፱ ፡ በሥነ ፡ ጥበብ ፡ ( በሳይንስ ) ፋክሊቲ ፡ ፺፪ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ባደረገው ፡ በሕግ ፡ ትምህርት፡ ፋክሊቲ ፡ ፺ ፤ በሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ (በአርት ) የማታ ፡ ትምህርት ፡ እርሱም ፡ ካለፈው ፡ ዓመት ፡ ከሁለት ፡ እጅ ፡ የበለጠ ፡ ሆኖ ፡ ፪፻ ፡ በብርሃንህ ፡ ዛሬ ፡ ነው ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ፻፵ ፡ ተማሪዎች ፡ ይገኛሉ ። በጠቅላላ ፡ ፳፻፷፩ ፡ ከሆነው ፡ ከተማሪዎቹ ፡ ቍጥር ፡ ውስጥ ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ አንዱ ፡ የቀን ፡ ተማሪዎች ፡ ሲሆኑ ፤ ሶስት ፡ መቶ ፡ ዘጠናው ፡ የማታ ፡ ተማሪዎች ፡ ናቸው።

ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡ ፲፪ ፡ የትምህርት ፡ ዓይነቶች ፡ በ፳፫ ፡ ክፍሎች ፡ ተከፍለዋል ። የትምህርት ፡ ደረጃ ፡ ወደ ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ መድረሱንና ፡ በየጊዜው ፡ እየበዛ ፡ የሚሄደውን ፡ የተማሪዎች ፡ ቍጥር ፡ ቦርዱ ፡ ተመልክቶ ፡ ለመጪው ፡ ዓመት ፡ ስድስት ፡ የሙሉ ፡ ጊዜ ፡ መምህራን ፡ እንዲቀጠሩ ፡ አድርጓል ። ከነዚህም ፡ አምስቱ ፡ የዶክተርነት ፡ ማዕርግ ፡ የያዙ ፡ ናቸው ።

የዩኒቬርስቲ ፡ ኮሌጅ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ የሳይንስ ፡ መመርመሪያው፡ ክፍል ፡ እየተስፋፋ ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ ለ፲፱፻፷፰፡ ዓ ፡ ም ፡ በቀረበው ፡ ባጀት ፡ ላይ፡ ለመጻሕፍትና ፡ ለሳይንስ ፡ መሣሪያዎች ፡ አስፈላጊው ፡ ገንዘብ ፡ ተመድቦአል ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለተደረሱ ፡ ጽሑፎችና ፡ ለሙዚየም ፡ በቂ ፡ ገንዘብ ፡ በተለይ ፡ ታስቦ ፡ ባጀቱ ፡ ተመድቦአል ።

ለኮሌጁ ፡ ትምህርት ፡ ስማቸውን ፡ ከሚሰጡት ፡ ተማሪዎች ፡ በላይ ፡ የኢዱኬሽን ፡ ፋክሊቲ ፡ ተቋቁሞ ፡ ወደፊት ፡ በየዓመቱ ፡ ፳፫ ፡ እጩ ፡ መምህራን ፡ ኮሌጁ ፡ እንዲቀበል ፡ አስፈላጊው ፡ ተደራጅቷል ። እነዚህም ፡ እጩ ፡ መምህራን ፡ ከአራት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የዲግሪን ፡ ማዕርግ ፡ ተቀብለው ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መምህራን ፡ ሆነው ፡ የሚመረቁ ፡ ናቸው ።

ስለ ፡ ሕንፃዎች ፡ ሥራ ፡ የዛሬ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ የታቀደው ፡ ፕሮ ግራም ፡ በፍጥነት ፡ እየተፈጸመ ፡ ሲሄድ ፡ ይታያል ። በዚህ ፡ ዓመት ፡ የሁ ለት ፡ ሕንፃዎች ፡ ሥራ ፡ በማለቅ ፡ ላይ ፡ ነው ። አንዱ ፡ ሕንፃ ፡ ለመቶ ፡ ተማሪዎች ፡ መኝታና ፡ ለደንበኛ ፡ ክሊንክ ፡ ጭምር ፡ ሲሆን ፡ ሁለተኛው ፡ ሕንፃ ፡ ለ፲፫ ፡ መምህራንና ፡ ለቤተ ፡ ሰቦቻቸው ፡ መኖሪያ ፡ የሚያገለግል ፡ ነው ።

ለተማሪዎች ፡ መኝታ ፡ እንደገና ፡ የሚሠራው ፡ ሕንፃ ፡ በቅርቡ ፡ ሊጀመር ፡ ነው ። ስለዚሁ ፡ ሕንፃ ፡ ማሠሪያና ፡ ለሚፈርሱ ፡ ቤቶች ፡ ስለሚ ከፈል ፡ ግምት ፡ ስለ ፡ እስፖርት ፡ ማስፋፊያ ፡ አስፈላጊው ፡ ገንዘብ ፡ ታስቦ በት ፡ ተመድቦአል ።

ግ ር ማ ዊ ፡ ሆ ይ ።

እነዚህ ፡ የተመለከቱት ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ የበላይ ፡ ጠባቂነትና ፡ መሪነት ፡ የሚካሄደውን ፡ የኮሌጁን ፡ ሕይወታዊነትና ፡ መስ ፋፋት ፡ አጉልተው ፡ የሚያሳዩ ፡ መሆናቸው ፡ አይጠረጠርም ። ስለከፍተ ኛውና ፡ ስለማያቋርጥ ፡ ቸርነትዎ ፡ በባለሥልጣኖች ፡ ቦርድ ፤ በመምህራ ኑና ፡ በተማሪዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ስም ፡ ሁኜ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋና ፡ ለማቅረብ ፡ እንዲፈቀድልኝ ፡ በትሕትና ፡ እለምናለሁ ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፤
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፤
ዕድሜ ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፤
ኢትዮጵያ ፡ በነፃነቷ ፡ ትኑር ።

❊ ❊ ❊

ለ) ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተናገሩት ፡ መሪ ፡ ቃል ።

ዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጃችን ፡ በተቋቋመ ፡ በአምስት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ በትጋት ፡ እየሠራ ፡ ባለማቋረጥና ፡ በኅብረት ፡ እያደገ ፡ መሄዱን ፡ ስንመለከት ፡ ሁላችንም ፡ የዚህ ፡ ደስታ ፡ ተካፋዮች ፡ ነን ።

ለኢትዮጵያ ፡ እድገት ፡ በዘረጋነው ፡ ፕላን ፡ ላገር ፡ ትልቅነት ፡ መሠ ረት ፡ ያደረግነው ፡ ትምህርትን ፡ ነው ። ከፍተኛ ፡ ትምህርትን ፡ የማዳረስ ፡ ጉዳይ ፡ ዘወትር ፡ ከአሳባችን ፡ አልተለየም ። ዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጃችን ፡ ገና ፡ ሕፃን ፡ ነው ። ወደፊት ፡ ግን ፡ የጥበብ ፡ ምንጭ ፡ በሆኑት ፡ በሌሎች ፡ ትም



ህርት ፡ ቤቶች ፡ መካከል ፡ የሚገባውን ፡ ሥፍራ ፡ በየጊዜው ፡ የሚይዝ ፡ ለመ ሆኑ ፡ እምነታችን ፡ ሙሉ ፡ ነው ።

ከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ባንድ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ አርአያ ፡ የሚሆኑ፡ ነገሮችን ፡ ማቋቋም ፡ ተግባሩ ፡ ነው ። እናንተም ፡ በመልካም ፡ መሪነት ፡ ስለተመራችሁ ፡ ዕውቀት ፡ የመፈለግን ፡ ምሳሌ ፡ አሳይታችኋል ። እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ለመግባባት ፤ የየራሳችሁን ፡ እውነተኛ ፡ አሳብ ፡ ለመግለጽ ፡ የሌሎችን ፡ አስተያየት ፡ ለመመርመርና ፡ ለመቅሠም ፡ በመከባበር ፡ ላይ ፡ በተመሠረተ ፡ ጥልቅ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ለመረዳዳት ፡ ስትጥሩ ፡ አርአያ ፡ የሚሆን ፡ ነገር ፡ ማቋቋማችሁ ፡ ነው ። በአገራችሁ ፡ ውስጥ ፡ እያደጋችሁ ፡ ባህሉን ፡ ሳትረሱ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገርም ፡ ለትምህርት ፡ ስትላኩ ፡ ሕዝብን፡ ለማገልገል ፡ ስትዘጋጁ ፤ አሁኑኑ ፡ በምትሠሩት ፡ ሥራ ፡ እናት ፡ አገራች ሁን ፡ የምታስደስትና ፡ ሀብታም ፤ ጸጥታዋም ፡ የተሟላ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ተካፋዮች ፡ ሆናችኋል ። የከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች፡ ዓላማ ፡ በሰውም ፡ በትምህርትም ፡ ከፍ ፡ ላለው ፡ መሠረታዊ ፡ ነገር ፡ ም ሳሌ ፡ የሚሆኑ ፡ የተመረጡ ፡ ፀዋቂዎችን ፡ ማደራጀት ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ለማድረግ ፡ አንዳንድ ፡ መሠረታዊ ፡ ነገሮችን ፡ አስቀድሞ ፡ ማቋቋም ፡ ያስ ፈልጋል ።

ለኢትዮጵያ ፡ የሚያስፈልጋት ፡ እውነተኛ ፡ ትምህርት ፡ የኑሮ ፡ ዘዴና፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ ጥበብ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የወጣቶቹን ፡ የመንፈሳዊ ፡ ዕውቀት ንም ፡ ያገር ፡ ልማድንም ፡ ማክበር ፡ ጭምር ፡ የሚያጕለምስ ፡ መሆን ፡ አለ በት ፡ ብለን ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ተናግረናል ። በትምህርት ፡ አሠልጣኞች ፡ ላይ ፡ የጣልንባቸው ፡ እጥፍ ፡ ተግባር ፡ ትምህርትን ፡ እንዲያስተምሩ ፡ ደግ ሞም ፡ የተማሪዎቻቸውን ፡ የተፈጥሮ ፡ ባሕርይ ፡ እንዲያንጹ ፡ ነው ።

በትምህርት ፡ ረገድ ፡ ካቀድናቸው ፡ ዓላማዎች ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ በዩኒ ቬርሲቲ ፡ ኮሌጃችን ፡ ተፈጽመው ፡ በማየታችን ፡ ደስታ ፡ ይሰማናል ።

የአርትና ፡ የሳይንስ ፡ ክፍል ፡ ተገናኝተው ፡ ባንድነት ፡ ሲመሩ ፡ ተማሪ ዎቹ ፡ ሁሉ ፡ አእምሮ ፡ አሠልጣኝ ፡ የሆነውን ፡ የአሳብ ፡ ትምህርት ፡ ከፕ ራቲክ ፡ ሥራ ፡ አዋሕደው ፡ እንደሚያስማሙ ፡ ሲደረግ ፤ የሳይንስ ፡ የሕግና፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥልቅ ፡ የሆኑትን ፡ ትምህርት ፡ ዓይነቶች ፡ ከማኅበራዊና ፡ ከ መንፈሳዊ ፡ ጥቅማቸው ፡ ጋር ፡ ተምረው ፡ እንዲያጠኑ ፡ መደረጋቸውን ፡

ስናይ ፡ ኢንዱስትሪም ፡ የሚወለደው ፡ ከዚህ ፡ ምንጭ ፡ ስለሆነ ፡ ስለመጭ ዎቹ ፡ ዘመናት ፡ የምናደርገው ፡ ተስፋ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ይሆናል ።

ተማሪዎች ፡ ለዚህ ፡ ከፍተኛ ፡ ሥራ ፡ የሚዘጋጁበት ፡ ትምህርት ፡ ለጊ ዜው ፡ በዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጆችን ፡ በመገኘቱ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸውንና ፡ የተሰ ጡትን ፡ ተግባሮች ፡ ለማከናወን ፡ የሥራ ፡ ዘዴን ፡ የባሕርይ ፡ ገንዘባቸው ፡ ያደረጉ ፡ ተማሪዎችን ፡ አስገኝቶ ፡ ለማሳየት ፡ በቅቶአል ።

ከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ ተሠርቶ ፡ ሲገኝ ፡ ሊሰጥ ፡ የሚ ችለውን ፡ እርዳታ ፡ መርሳት ፡ አይገባንም ። ሴቶች ፡ ልጆች ፡ በዕድሜ ፡ ሳይ ገፉ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ እየተዉ ፡ ንብረት ፡ ለመያዝ ፡ በመቻኮላቸው ፡ ወደ ፡ ዐቀድነውና ፡ ለወደፊቱም ፡ ለምናቅደው ፡ የትምህርት ፡ ዓላማ ፡ ለመ ድረስ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ የሚቻል ፡ አይመስልም ፡ ብለን ፡ መሥጋታችንን ፡ ከጥቂት ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ መግለጽ ፡ ግድ ፡ ሆኖብን ፡ ነበር ። በዚህም ፡ ረገድ ፡ ወላጆች ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ የአሳባችን ፡ ተቀባዮችና ፡ ረዳቶቻችን፡ እንዲሆኑ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ ይልቅ ፡ የዛሬው ፡ ሁኔታ ፡ በጣም ፡ ተሻሽሎ ፡ ይገኛል ። ኢትዮጵያውያን ፡ አባትና ፡ እናቶች ፡ በብዙ ፡ ሺህ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሴቶች ፡ ልጆችን ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሲልኩ ፡ ይታያሉ ። ከሴቶች ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ በከፍተኛ ፡ ትምህ ርት ፡ ቤቶችና ፡ በዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ የሚገቡት ፡ ቍጥር ፡ እየበዛ ፡ በመ ሄዱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደስታ ፡ ይሰማናል ።

አንድነትን ፡ በማጕልመስ ፡ ለሕዝብ ፡ መሪዎችና ፡ ቅን ፡ አገልጋዮች፡ የሚሆኑ ፡ ዐዋቂዎችን ፡ ለማስገኘት ፡ ቤተ ፡ ሰብን ፡ የጠነከረና ፡ የተደሰተ፡ በዕውቀትም ፡ የገፋ ፡ ለማድረግ ፡ የሚችሉ ፡ ሰዎችን ፡ ለማስገኘት ፡ ከፍተ ኛውን ፡ ትምህርት ፡ ያገኙ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የራሳቸውን ፡ ጥቅም ፡ በመተው፡ መሥዋዕት ፡ ማድረግ ፡ አለባቸው ።

ማናቸውም ፡ ሞያ ፡ ቢሆን ፡ የራስን ፡ መሥዋዕትነት ፡ ይጠይቃል ። በፊዚክ ፡ ዕውቀት ፡ ቢሆን ፡ ትዕግሥትንና ፡ ጠንክሮ ፡ መሥራትን ፡ ይጠይ ቃል ። በሕግና ፡ በኤኮኖሚ ፡ ቢሆን ፡ የራስን ፡ ጥቅም ፡ ትቶ ፡ ለጠቅላላው ፡ የአገር ፡ ጥቅም ፡ ማሰብን ፡ ይጠይቃል ። በሕክምና ፡ ረገድ ፡ ከልብ ፡ ያለፈ ፡ መሰናዳትንና ፡ ቅናትን ፡ የወደፊት ፡ አላፊነትንና ፡ ዘወትር ፡ ለሥራው ፡ ታማኝ ፡ ሆኖ ፡ መገኘትን ፡ ይጠይቃል ። የማስተማር ፡ ሞያም ፡ ቢሆን ፡ ይህ



ንኑ ፡ የመሰለ ፡ መሥዋዕትነትን ፡ ይጠይቃል ።

እናንት ተማሪዎች ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ አገር ፡ ወጣቶች ፡ ሁሉ ፡ እናን ተም ፡ መሻሻልንና ፡ ታላላቅ ፡ ነገሮችን ፡ ለመሥራት ፡ ትመኛላችሁ ። ነገር፡ ግን ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ምኞታችሁን ፡ የአንድ ፡ ትውልድ ፡ ዘመን ፡ ሊፈጽመው ፡ አይችልም ። እንደምኞታችሁ ፡ ወይም ፡ ከምኞታችሁ ፡ እን ዲበልጥ ፡ አድርጋችሁ ፡ በሚገባ ፡ የመራችሁት ፡ እንደሆነ ፡ በየዕድላችሁ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሞያ ፡ ከመያዝና ፡ በአስተማሪነት ፡ ሥራችሁ ፡ የሚገኘው ፡ ፍሬ ፡ ብዙ ፡ ሺህ ፡ ወጣቶች ፡ ላይ ፡ እየተባዛ ፡ ይሄዳል ።

የባለሥልጣኖችን ፡ ቦርድና ፡ ፕሬዚዳንቱን ፡ በዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ፋክሊቲ ፡ የሚገኙትንም ፡ መምህራን ፡ በሥራቸው ፡ እናመ ሰግናቸዋለን ።

እናንተም ፡ ወጣቶች ፡ በዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ የዲግሪ ፡ ማዕርግ ፡ ለመ ቀበል ፡ ስለበቃችሁ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ብሎናል ።

---

# 498

የአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ለዕረፍት ፡ በሚዘጉበት ፡ ቀን ፡ ሐምሌ ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከእኩለ ቀን ፡ በኋላ፡ በ፱ ፡ ሰዓት ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ግቢ ፡ በልደት ፡ ሜዳ ፡ አዳራሽ ፡ ተገኝተው ፡ ከ ፶፮ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በፈተና ፡ ብልጫ ፡ ላገኙት ፡ ወጣቶች ፡ ሽልማት ፡ ሲሰጡ ፡ ትምህርታቸ ውን ፡ ለጨረሱትም ፡ ወጣቶች ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ሲሰጡ ፡ የትምህርትና ፡ የሥነ ፡ ጥበብ ፡ ም ሚኒስትር ፡ ክቡር ፡ አቶ ፡ አካለ ፡ ወርቅ ፡ ሀብተ ፡ ወልድ ፡ በግርማዊነታቸው ፡ ፊት ፡ ያደረጉት ፡ ንግ ግር ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡

ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡

ል ዑ ላ ን ፡

ክ ቡ ራ ን ።

በግርማዊነትዎ ፡ ቸርነት ፡ ትምህርትን ፡ እየተመገቡ ፡ የሚያድጉት ፡ ዕድለኞቹ ፡ ወጣቶችዎ ፡ የትምህርት ፡ ቤቶቹ ፡ ስለክረምቱ ፡ ለዕረፍት ፡ በሚ ዘጉበት ፡ የትምህርት ፡ ቤታቸውን ፡ ፕሮግራም ፡ የጨረሱ ፡ የምስክር ፡ ወ ረቀት ፡ በፈተና ፡ አንደኛና ፡ ሁለተኛ ፡ የሆኑት ፡ ሽልማታቸውን ፡ ለመቀ

በል ፡ በድምሩ ፡ ፩ሺ፮፻፹፪ ፡ ወጣቶች ፡ ቀርበዋል ።

## ግ ር ማ ዊ ፡ ሆ ይ ።

ትምህርት ፡ የማይማረክና ፡ የማይደመሰስ ፡ መሣሪያ ፡ መሆኑን ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ተመልክቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ በትምህርት ፡ የሚጐለምሱበት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በአገር ፡ ውስጥ ፡ ከአቋቋመና ፡ ወደውጭ ፡ አገርም ፡ ተማሪዎችን ፡ መላክ ፡ ከጀመረ ፡ ወዲህ ፡ በየጊዜው ፡ የተገኘው ፡ ፍሬ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ውጤትን ፡ ሰጥቶአል ።

ትምህርት ፡ የአእምሮ ፡ መክፈቻ ፡ ቍልፍ ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ የትምህርት ፡ ፈላጊዎች ፡ ቍጥር ፡ በየዘመኑ ፡ እየጨመረ ፡ ራሱን ፡ በትምህርት ፡ ለማሳደግ ፡ የማይጣጣር ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የለም ። "እግዚአብሔር ፡ ሳያዳላ ፡ የፈጠረውን ፡ አእምሮ ፡ ሥራ ፡ ማስፈታት ፡ ለድንቍርና ፡ መገዛት፡ ነው ፡" የተባለው ፡ ንጉሣዊ ፡ ቃል ፡ በያንዳንዱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ አእምሮ ፡ ተቀርጾ ፡ ሁሉንም ፡ ወደ ፡ ዕውቀት ፡ ጐዳና ፡ ይመራዋል ።

በየትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የሚሰጠው ፡ ትምህርት ፡ የቀለም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ ትምህርት ፡ ከሌላውም ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ በበለጠ፡ ስለተስፋፋ ፡ በእጅ ፡ ሥራ ፡ ትምህርት ፡ ወጣቶች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እርምጃ ፡ አድርገዋል ።

የትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ቍጥር ፡ እየጨመረ ፡ ስለሄደ ፡ በመሥራትም ፡ ላይ ፡ ከሚገኙት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ የሚበልጡት ፡ ሙሉ ፡ ድርጅት ፡ በማግኘታቸው ፡ ተጨማሪ ፡ ተማሪዎችን ፡ ለመቀበል ፡ ተችሏል ።

አሁን ፡ ባሉት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ለሙሉ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ወጣቶች ፡ ትምህርትን ፡ ለማዳረስ ፡ የሚያዳግት ፡ ቢሆንም ፡ በግርማዊነትዎ ፡ የተዘረጋው ፡ የትምህርት ፡ ፕላን ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ እያደገ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ ትምህርትን ፡ ለማዳረስ ፡ መንገድ ፡ ይዟል ። በትምህርት ፡ ያደጉት ፡ ወጣቶች ፡ ቍጥር ፡ እየበዛ፡ በመሄዱ ፡ የሚበልጡት ፡ የሥራ ፡ ክፍሎች ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ይመራሉ ። ለማስረጃ ፡ ያህል ፡ በትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ እንኳ ፡ የመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ እንዲመሩ ፡ የተደረገው ፡ ሥራ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ በመሆኑ ፡ በዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲቀጥል ፡ ተደርጎአል ።

የአገሩ ፡ ኤኮኖሚ ፡ ከፍ ፡ በማለቱ ፡ የንግድ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ማስ



ፋፋት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነ ። ለንግድ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሕንፃ ፡ ማሠሪያም ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በፈቀደልን ፡ ገንዘብ ፡ ሥራው ፡ ፍጻሜ ፡ እንዳገኘ ፡ ቍጥራቸው ፡ የበዛ ፡ ተማሪዎችን ፡ ለመቀበል ፡ ታስቦአል ።

የመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ መምህራን ፡ ብቻ ፡ እንዲመሩ ፡ ለማድረግ ፡ ከያዝነው ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ፡ በየዓመቱ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ መምህራን ፡ እየወጡ ፡ ከሰባት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የአንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ መምህራን ፡ እንዲካሄዱ ፡ ተወስኖአል ።

እንደዚሁም ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ እንዲካሄዱ ፡ ታስቦ ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርትን ፡ የጨረሱ ፡ ወጣቶችና ፡ በማስተማር ፡ ከቈዩት ፡ መምህራን ፡ በፈተና ፡ እየተመረጡ ፡ በዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ የአራት ፡ ዓመት ፡ ትምህርት ፡ ተከታትለው ፡ የዲግሪ ፡ ማዕርግ ፡ እያገኙ ፡ ከአራት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ በየዓመቱ ፡ ከኻያ ፡ አምስት ፡ መምህራን ፡ በላይ ፡ በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ እንዲያስተምሩ ፡ ተወስኖአል ።

የመሐንዲስ ፡ ኮሌጅም ፡ እንደ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ ከሚመጣው ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ የአራት ፡ ዓመት ፡ ትምህርት ፡ አዘጋጅቶ ፡ የመሐንዲስነት ፡ ዲግሪ ፡ ያላቸውን ፡ ወጣቶች ፡ መስጠት ፡ ይጀምራል ።

በሐረር ፡ የሚሠራው ፡ የእርሻ ፡ ኮሌጅ ፡ ሙሉ ፡ ድርጅቱ ፡ በቅርብ ፡ ስለሚያልቅ ፡ ጅማ ፡ ባለው ፡ የርሻ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተደርበው ፡ የርሻ ፡ መሐንዲስነት ፡ የሚማሩት ፡ ወጣቶች ፡ በሚከተለው ፡ ዓመት ፡ ይዛወራሉ።

በግርማዊነትዎ ፡ ፈቃድ ፡ እንዲቋቋም ፡ የታዘዘው ፡ የሕንፃ ፡ መሐንዲስ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሥራው ፡ ከፍጻሜ ፡ ስለተዳረሰ ፡ የ፪ኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ የጨረሱ ፡ ወጣቶች ፡ በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በመስከረም ፡ ትምህርት ፡ ይጀምሩበታል ።

የትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ ድርጅት ፡ በዝርዝር ፡ በመግለጥ ፡ የግርማዊነትዎን ፡ ጊዜ ፡ ማባከን ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ የከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ ሁኔታ ፡ ብቻ ፡ ለማስታወስ ፡ ያህል ፡ በአጭሩ ፡ ገለጥኩ ።

የመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ለሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ለከፍተኛ ፡ ትምህ